አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 180 የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# «በሴቶች ላይ ከሚደርሰው የችግር አዙሪት ለመውጣት ቁልፉ ጉዳይ የሴቶች መደራጀት ነው»

- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

አማን ረሺድ



አዲስ አበባ፡- በሴቶች ላይ ከሚደርሰው የችግር አዙሪት ለመውጣት ቁልፉ ጉዳይ የሴቶች መደራጀት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ፡፡

ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ተኛ እንዲሁም በኢትዮጵያ ለ47ተኛ ጊዜ የተከበረውን የሴቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ ባስተላለፉት መልዕክት በሴቶች ላይ ከሚደርሰው የችግር አዙሪት ለመውጣት ሴቶች መደራጀት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በጾታ መሠረት አድርገው የሚደርሱ ችግሮችን ለመቅረፍ በተናጠል ከመታገል ይልቅ ሴቶች ጠንካራ የጋራ አጀንዳ ሊይዙ ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የሴቶችን መብት ለማስከበር ሁሉም የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በመልዕክታቸው በሴቶች ላይ የሚደርሱ አድሎ፣ መገለልና ጥቃት ወይም ማንኛውም አካላዊም ሆነ ሥነ ልቦናዊ ጥቃቶች ካለምንም የሀብት፣ የትምህርት፣ የሥልጣን፣ የዕድሜ፣ የዘር፣ የሃይማኖትና የአስተሳሰብ ልዩነቶች በሁሉም ሴቶች ላይ ይቃጣሉ። ጉዳቱ የሚያደርሰው ጥፋት ይለያይ ይሆናል እንጂ የትኛዋም ሴት አጋጥሟል ብለዋል።

ሁሌም እንደምለው የሴቶች ቀን በዓመት አንድ ቀን የሚታወስ ሳይሆን የ365 ቀናት ሥራ መሆን አለበት ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ያለፍነውን፣ እየኖርን ያለነውንና የወደፊቱን ከሴቶች እኩልነት፣ ተጠቃሚነት ከሰው ልጅ መብት አንጻር እንድንቃኝ አስታዋሻችን፤

"በሴቶች ላይ ከሚደርሰው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# «ኢትዮጵያ ብዙና አመቺ የኢንቨስትመንት አማራጮች ያሏት አገር ነች»

- የፓኪስታን ኢንቨስተሮች

መስከረም ሰይፉ




ፎቶ ፡- ሃዲስ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ከሌሎች አገራት በተሻለ ብዙ አማራጮች ያሏት አገር መሆኗን በኢትዮጵያ ጉብኝት ያደረጉት የፓኪስታን ኢንቨስተሮች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገለጹ፡፡

የግሊትስ መድኃኒት ድርጅት ዳይሬክተር ቻውዳርይ ቢላል፤ በጉብኝቴ ኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይ ከመሆናቸው በተጨማሪ አገሪቱ ለኢንቨስትመንት የምትመች አገር መሆኗን ተመልክቻለሁ ብለዋል፡፡

ድርጅታቸው ግሊትዝ ፋርማሲ በዓለም ላይ ከአምስት መቶ በላይ ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በበርካታ የአፍሪካ አገራት ቅርንጫፎችን ከፍቶ

«ኢትዮጵያ ብዙና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ሲዳማ ባንክ
Sidama Bank
Bank for All!
ባንካችን የተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ቅድመ-ሁኔታዎችን አጠናቅቆ በቅርቡ ሥራ ለመጀመር መዘጋጀቱን ስንገልፅ በታላቅ ደስታ ነው
አድራሻ
+25146 220 4704
+251944119303
565
+251462204704
info@sidamabanksc.com
www.sidamabanksc.com
ሲዳማ ባንክ አ.ማ.
Sidama Bank S.C.
የሁሉም ባንክ!

## ሴቶች በትምህርት ዘርፍ እኩል የመሳተፍ ዕድል እንዲፈጠርላቸው እየተሠራ ነው

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- ሴቶች በትምህርት ዘርፍ እኩል የመሳተፍ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የሚረዳ ሥራ እያከናወነ መሆኑን የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ሴቶች በትምህርት ዘርፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢትዮ ቴሌኮም

ለመዲናዋ የመንገድ ጽዳት ሴት ሠራተኞች ዘመናዊ የስልክ ቀፎ አበረከተ

ገጽ 4

AMG STEEL FACTORY
ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
Our Products
GI-Coil Color Coil Tiles
Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories
Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC
ETHIOPIA
Our Products
Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Steel Structure Tanker
Akaki, Gelan
0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

# በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ7 ሺህ በላይ ሴቶች በማህጸን ካንሰር ይያዛሉ

## - የሴቶች ቀንን አስመልክቶ የጡትና የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ ተደረገ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ7 ሺህ በላይ ሴቶች በማህጸን በር ካንሰር እንደሚያዙ ጤና ሚኒስቴር ገለጸ። ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን አስመልክቶ በመዲናዋ የጡትና የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ ተደረገ።

‹‹የላቀ ትኩረትና ቁርጠኝነት ለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት›› በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ቸርቸል ጤና ጣቢያ የሴቶች ቀን ትናንት ተከብሯል።

በጤና ሚኒስቴር የካንሰር አስተባባሪ ሲስተር ታከለች ሞገስ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በዓመት ከ7 ሺህ በላይ ሴቶች በካንሰር በሽታ ይጠቃሉ፡፡ በማህጸን በር ካንሰር ከሚጠቁት ከ7 ሺህ በላይ ሴቶች ከ5 ሺህ በላይ የሚሆኑት በበሽታው ሕይወታቸው ያልፋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ አስተባባሪዋ እንደተናገሩት፣ የካንሰር በሽታ 67 በመቶ የሚጎዳው ሴቶችን ነው፡፡ በዚህም 50 በመቶ የሚሆነው የማህጸን በር ካንሰር እና የጡት ካንሰር ነው፡፡

አስተባባሪዋ እንደተናገሩት፤ የካንሰር በሽታ 67 በመቶ የሚጎዳው ሴቶችን ነው፡፡ ከዚህም 50 በመቶ የሚሆነው የማህጸን በር ካንሰር እና የጡት ካንሰር ነው፡፡

በዓለማችን ከ600ሺህ በላይ ሴቶች በማህጸን በር ካንሰር ይጠቃሉ ያሉት ሲስተር ታከለች፤ ከተጠቁት ውስጥ ከ300 ሺህ በላይ የሚሆኑት ሕይወታቸውን ያጣሉ፡፡ ከሚሞቱት መካከል ደግሞ 90 በመቶ ያህሉ ኢትዮጵያን ጨምሮ ባላደጉ አገራት የሚገኙት ዜጎች ናቸው ብለዋል፡፡

ሲስተር ታከለች እንዳስታወቁት፤ ጤና ሚኒስቴር እነዚህን በሽታዎች ለመከላከል በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህም በአጠቃላይ በአገሪቱ ከ1ሺህ 300 በላይ የጤና ተቋማት የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ ይሰጣል። በአዲስ አበባ ከተማም ሁሉም የመንግሥት የህክምና ተቋማት አገልግሎቱ ለተጠቃሚዎች እየቀረበ ይገኛል።

ማንኛዋም ዕድሜዋ ከ30 እስከ 49 የሆነች ሴት የጡት እና የማህጸን ካንሰር ምርመራ በማድረግ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባት መልዕክት አስተላልፈዋል።

ካንሰር በብዛት ሴቶችን እየገደለ ያለ በሽታ ነው ያሉት አስተባባሪዋ፤ የሴቶችን ቀን አስመልክቶ ምርመራ በመዘጋጀቱ ሴቶች በአንድ ጊዜ የጡትና የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ እንዲያከናውን ዕድል ፈጥሯል ብለዋል።




# በግብርናው ዘርፍ ሆርቲካልቸር ከቡና ቀጥሎ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት ሆኗል

## - ዘርፉ ባለፉት ሰባት ወራት 414 ሚሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ሆርቲካልቸር ከቡና ቀጥሎ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት ዘርፍ መሆኑ ተገለጸ፡፡ ባለፉት ሰባት ወራት ብቻ ከዘርፉ 414 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማህበር አዘጋጅነት የሚካሄደው ስምንተኛው የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ (ሆርቲካልቸር) ዓለም አቀፍ ኤክስፖ ትናንት በሚሊኒየም አዳራሽ ተከፍቷል፡፡ በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ፤ በአሁኑ ወቅት በግብርናው ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ ግኝት መሠረት የሆነው የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ አዲስ እያዘጋጀ ባለው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ትኩረት መስጠቱንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ከቡናና ሌሎች ኤክስፖርት ከሚደረጉ ምርቶች አንጻር የአበባ ዘርፍ ሁለት አስርት ዓመታት ያህል ዕድሜ ያለው ቢሆንም፤ ባጠረ ጊዜ ውስጥ በአነስተኛ ቦታ ላይ ጥሩ ውጤት እያሳየ መጥቷል፡፡ የአገሪቱ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛው ትልቁ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት ሆኗል፡፡

በዘርፉ ባለፉት ሰባት ወራት ብቻ 414 ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ውስጥ አበባ ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝና አትክልትና ፍራፍሬም ትልቅ ለውጥ እያሳየ ያለ ሴክተር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ዘርፉ ከውጭ ምንዛሬ ግኝቱና ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ ሲታይ በእርሻ ኢንቨስትመንት በውስን ቦታዎች ሰፊ የሥራ ዕድል እየተፈጠረ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ መንግሥት አዲስ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ አዘጋጅቶ እያጠናቀቀ ሲሆን፤ በፖሊሲው ውስጥ የተካተቱትን አዳዲስ እሳቤዎች መተግበር ተጀምሯል፡፡ በፖሊሲው ውስጥ ትልቅ ትኩረት ካገኙት ጉዳዮች አንዱ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ካላት አግሮኢኮሎጂና የአየር ንብረት አንጻር የአትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶች ከየትኛውም አገር የተሻለ እምቅ ሀብት ነው፡፡

የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ፤ የግብርና አምዶች በሆኑት በምግብ ዋስትና ራስን መቻል፣ ወጪ ምርትን መጨመር፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ እያሳየ ያለው ሂደት አበረታች እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የተዘጋጀው ኤክስፖም ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ያላትን እምቅ አቅም ለማስተዋወቅና ዓለምአቀፍ የገበያ ትስስርን ለመፍጠር፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን ለማሳደግ እንዲሁም የተወዳዳሪነት አቅምን ለማጎልበት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው በበኩላቸው፤ ሴክተሩ የኢንቨስትመንት ዕድልን የሚያመጣና አገራዊውን ኢኮኖሚ የሚደግፍ በመሆኑ አየር መንገዱ በካርጎ አገልግሎቱ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ምርትን ለተለያዩ የዓለም አገራት በማቅረብ ዓለም አቀፍ የገበያ ትስስር እንዳይቋረጥ ጉልህ ሚና እየተወጣ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

በኤክስፖው ላይ የምርምር እና የትምህርት ተቋማቶችን ጨምሮ በአበባ፣ በአትክልት እና ፍራፍሬ ማምረት ላይ የተሰማሩ፤ በግብዓት አቅርቦት በማዳበሪያ፣ በኬሚካል፣ በግሪን ሀውስ፣ የግብርና ዕቃዎች አቅርቦት ላይ የተሰማሩ እንዲሁም በአግሮሎጂስቲክስ አገልግሎት አቅርቦት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችና አማካሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተሰብስቧል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በበጋ መስኖ ስንዴ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር የተሸፈነ ሲሆን፣ ከ83 ሺ ሄክታር ላይ እስካሁን 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ መሰብሰብ መቻሉን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከሦስት ዓመት በፊት በስንዴ ሰብል የሚሸፈነው መሬት አሁን ከሚሸፈነው መሬት ጋር ሲነጻጸር ትልቅ ልዩነት አለው፡፡ በ2012 እና በ2013 ዓ.ም ስምንት መቶ ሺ ሄክታር ገደማ በስንዴ ሰብል ይሸፈን ነበር፡፡ በዘንድሮው 2014/2015 የምርት ዘመን አንድ ሚሊዮን 744 ሺ ሄክታር በስንዴ ሰብል እንዲሸፈን ተደርጓል፡፡ ስንዴን በክረምቱ ብቻ ሳይሆን በበጋ መስኖ መመረት ስላለበት በ2012 በጀት ዓመት በ7 ሺ ሄክታር ላይ በበጋ መልማት የጀመረ ሲሆን አሁን ላይ ትልቅ የአገር የልማት አጀንዳ ሆኖ እየተሠራበት ነው፡፡

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በዘንድሮው ዓመት አንድ ሚሊዮን ሄክታር በበጋ መስኖ ስንዴ እንዲለማ ታቅዶ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ሰብል መሸፈን ተችሏል፡፡ በበጋ መስኖ ከተሸፈነው የስንዴ ሰብል በሔክታር የሚጠበቀው ከ38 ነጥብ 5 እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ነው፡፡ በመኸርና በበጋ መስኖ አጠቃላይ በክልል ከመቶ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ምርት ይመረታል፡፡

እንደ አገር በትኩረት እየተሠራበት ያለው ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት መተካት መሆኑን የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ እንደአገር የተያዘውን አቅጣጫ በማሳካት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ምርት ማስቀረት ተችሏል፡፡

እንደ ክልል የስንዴ ምርትን ለማሳደግ ከአስር እስከ 15 ሚሊዮን ኩንታል ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው፡፡ ባለፈው ወር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባስጀመሩት መርሃ ግብር ባሌ ላይ የስንዴ ምርት ለውጭ ገበያ መቅረቡን አቶ ጌቱ ገልጸዋል፡፡

ስንዴን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የገለጹት አቶ ጌቱ፤ በዚሁ መሠረት በኦሮሚያ ክልል የበጋ መስኖ ስንዴ እየተሰበሰበ ነው፡፡

የምርት እጥረት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌለ የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ የበጋ ስንዴ ልማት ሥራውን አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሮች በከፍተኛ ተነሳሽነት እየሠሩ ነው ብለዋል፡፡


ፎቶ - በገባው ገብሬ

አቶ ጌቱ ገመቹ

ዜና

# ለልማት ሥራው ምሉዕነት የሴቶች ድርሻ የላቀ መሆኑ ተገለጸ

**መክሊት ወንድወሰን**


ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

አዲስ አበባ፡- በተሰማሩበት የትኛውም መስክ ውጤታማ መሪ የመሆን ተፈጥሯዊ አቅም ያላቸው በመሆኑ ለአገራዊ ልማቱ ምሉዕነት የሴቶች ድርሻ ተኪ እንደሌለው ተገለጸ፡፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ ለ112ኛ እንዲሁም በአገርአቀፍ ደረጃ ለ47ኛ ጊዜ የተከበረው የሴቶች ቀን በትናንትናው ዕለት በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያዩ ዝግጅቶች በድምቀት ተከብሯል፡፡

በዝግጅቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርትና የመጀመሪያዋ ሴት የኮሌጅ ዲን ዶክተር አዲስዓለም አባትሁን ባደረጉት ንግግር፤ መሪነት ለሴቶች በተፈጥሮ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡ ሴቶች በተሰማሩበት የትኛውም መስክ ውጤታማ መሪ የመሆን ልዩ ተፈጥሯዊ አቅም ያላቸው በመሆኑ ሴቶችን ወደ አመራርነት ማምጣት ላይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል ብለዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በበኩላቸው ሴቶች የሌሉበት እና አሳታፊ ያላደረገ የሥራም ሆነ የልማት እንቅስቃሴ ምሉዕ ሊሆን እንደማይችል ጠቅሰዋል፡፡

ሴቶች በቤትም በሚሠሩበት ተቋምም ሆነ በአገር ደረጃ የጀርባ አጥንት ናቸው ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ሴቶችን በአመራርነት እና በውሳኔ ሰጪነት በማሳተፍ ተጨባጭ ሥራ እያከናወነ እንደሚገኝ አንስተዋል፡፡

የኢፕድ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት አስተባባሪ ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ፤ ከጥቂት ቀናት በፊት የተከበረው የዓድዋን ድል በዓል ሴቶች በከፍተኛ ቁርጠኝነት እና በአገር ወዳድነት የአገሪቱን ሰላም እና አንድነት ለማስጠበቅ የነበራቸው ሚና ማሳያ እንደነበር አውስተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ብርሃኔ ገለጻ፤ መንግሥት በተቋማት ውስጥ እንዲሁም በከፍተኛው የአገሪቷ ውሳኔ ሰጪ አካላት ዘንድ ሴቶች የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶችን ማድረጉን ጠቅሰው ሴቶችም የተሰጣቸውን ዕድል በአግባቡ እንደሚጠቀሙ በተለያዩ አውዶች እያስመሰከሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

«እኛ ሴቶች፤ እናቶች፣ እህቶች፣ ሚስቶችም ሆነን ትውልድን በመተካትም ሆነ በማነፅ ቀጣይ አገር ተረካቢ የማፍራቱን ድርሻ ከአጋሮቻችን ባልተናነሰ ደረጃ ኃላፊነት መወጣት ያለብን ከመሆኑም በላይ አሁን ለምንሻው ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር መስፈን ያላሰለሰ ኃላፊነቶች አሉብን» ሲሉም ገልጸዋል፡፡

«'እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ» በሚል መሪ ሃሳብ በዓለም ደረጃ ለ112ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ለ47ኛ ጊዜ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለስምንተኛ ጊዜ የተከበረው በዓል ላይ የተለያዩ መርሃግብሮች ተከናውነዋል፡፡

የሴቶች ቀንን አስመልክቶ በድርጅቱ ሴት ሠራተኞች ተዘጋጅቶ ለህትመት የበቃው የአዲስ ዘመን የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ልዩ ዕትም ምረቃ ከዕለቱ ዝግጅቶች አንዱ ነው፡፡ ልዩ እትሙ ስለሴቶች ጉዳይ ብቻ የያዘ ሲሆን የበርካታ ጠንካራ ሴቶች የሕይወት ተሞክሮን በውስጡ ያካተተ ነው፡፡


አቶ ፍቅረኢየሱስ አሸናፊ

# በሲዳማ ክልል በተፋሰስ ልማት ሥራ ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ይሳተፋሉ

- 116 ሺህ 384 ሄክታር መሬት ለማልማት እየተሠራ ነው
- በመጪው ክረምት ከ316 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

**በዳግማዊት ግርማ**

ሀዋሳ፡- በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተፋሰስ ልማት ሥራ ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ይሳተፋሉ ሲል የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ አስታወቀ። በክረምት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርም ከሦስት መቶ አስራ ስድስት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል መታቀዱም ተመላክቷል።

የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ፍቅረኢየሱስ አሸናፊ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ «የዘመነ የተፋሰስ ልማት ለብልጽግናችን» በሚል መሪ ሀሳብ ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት የተፋሰስ ልማት ሥራ እየተከወነ ሲሆን፣ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የሰባት በመቶ ዕድገት በማሳየት 116 ሺህ 384 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዷል።

ባለፈው ዓመት በተሰራው የኅብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ሥራ ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ነው ያሉት አቶ ፍቅረኢየሱስ ዘንድሮ እየተከናወነ ያለው የተፋሰስ ልማት ሥራ አስር ቢሊዮን ብር እንደሚገመት ገልጸዋል።

በክረምት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ከሦስት መቶ አስራ ስድስት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለማልማት መታቀዱንም አቶ ፍቅረኢየሱስ ተናግረዋል። የሌማት ትሩፋትን የሚያጎለብቱ አቡካዶ፤ ማንጎና አፐል የመሳሰሉ የፍራፍሬ ችግኞች መዘጋጀታቸውንም አክለው ገልጸዋል። ችግኞቹም ለሚያዝያና ሐምሌ የተከላ ሥራ እንደሚደርሱም ተናግረዋል።

የቡና ምርትን በስፋትና በጥራት ለማምረት እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት አቶ ፍቅረኢየሱስ የቡናን ለምነት የሚጨምሩ የዋንዛ፣ ብርብራና መሰል ችግኞችን የመትከል ሥራ እንደሚኖር ገልፀዋል።

አቶ ፍቅረኢየሱስ እንደገለፁት፤ ለምግብነትና ለደን ሽፋን የሚሆኑ ችግኞችን የመትከል ሥራ የሚሠራ ሲሆን ባህርዛፍን የሚተኩ ችግኞችን የመትከል ሥራን በማከናወን ለኅብረተሰቡ የሚጠቅም የደጋ፣ የወይናደጋና የቆላ ቀርከሀን በማምረት ስነምህዳርን የመጠበቅ ሥራ ለመሥራት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

የተፋሰስ ልማት በሲዳማ ክልል ለኅብረተሰቡ ዘርፈብዙ ጠቀሜታን ያስገኘ ነው፡፡ ምርትና ምርታማነት ጨምሯል፣ የአፈር መሸርሸርን መቀነስ ተችሏል፣ ምንም ዓይነት ሰብል የማያበቅሉ ድንጋያማ ስፍራዎች በተሠሩ ተደጋጋሚ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ማብቀል ችለዋል ሲሉ አቶ ፍቅረኢየሱስ አብራርተዋል ።



# የኮርፖሬሽኑ ገቢ በአራት እጥፍ ዕድገት አሳይቷል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ዓመታዊ ገቢ ባለፉት አምስት ዓመታት በአራት እጥፍ ዕድገት ማሳየቱ ተገለጸ። ኮርፖሬሽኑ ባለፉት አምስት ዓመታት ላከናወናቸው ስኬታማ ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ ባለድርሻ አካላት እውቅና ሰጥቷል።

የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የቦርድ ሰብሳቢና የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ እንደገለጹት፤ ባለፉት አምስት ዓመታት የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር በአሠራር፣ በጥገናና በአቅም ግንባታ ዘርፍ አመርቂ ስኬቶችን አሳይቷል። የአዲስ አበባ - ጅቡቲ የባቡር መስመር እያደገ ለመጣው የቻይና እና አፍሪካ ግንኙነት ትልቅ ምሳሌ ነው። ለወደፊትም ብሩህና ጠንካራ የኢትዮ ጅቡቲና ቻይና ግንኙነት ማሳደጊያ ሆኖ ይቀጥላል።

እንደ ገንዘብ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር የክዋኔ፣ የጥገና የአቅም ግንባታ ሥራዎች አከናውነዋል። በጭነት በኩል የማጓጓዝ አቅሙ በመቶ ፐርሰንት አድጓል። አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ቶን ጭነት በዓመት ማጓጓዝ ችሏል ያሉት አቶ አህመድ፤ የኩባንያው ዓመታዊ ገቢ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ባለፉት አምስት ዓመታት በአራት እጥፍ ዕድገት ያሳየ ሲሆን 2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ደርሷል ብለዋል።

እንደ ኢትዮ ጅቡቲ ዓይነት መሠረተ ልማትና ወሳኝ ሜጋ ፕሮጀክት ለኢትዮጵያም ሆነ ለጅቡቲ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የኮርፖሬሽኑ ስኬት ቀጣናዊ ውህደትን ለማጠናከር፣ የሎጂስቲክስ ዘርፉን ለመቀየር፣ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ለማስተዋወቅ፣ የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ባለሀብቶችን ለማበረታታት ይረዳል ነው ያሉት።

አቶ አህመድ፤ በቀጣይ የባቡር መስመሩ ከፍተኛ አቅሙን በማሳደግ ፈጣን፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ የእቃ ማጓጓዣ አገልግሎት በመስጠት ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ምርጡ የትራንስፖርት አማራጭ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ጅቡቲና ኢትዮጵያ የሕዝብ ለሕዝብ ውህደት መፍጠር የባቡር መስመር ሊሳካ የሚገባው ግብ እንደሆነ ጠቁመዋል።

የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አብዲ ዘነበ (ዶክተር) እንደገለጹት፣ የኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር የሁለቱን አገሮች የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በከፍተኛ ደረጃ አሳድጓል። ምድር ባቡሩ በማዕድንና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ምርቶችን በማጓጓዝ ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ በኢትዮጵያ በድርቅና በሌሎች ምክንያቶች ለተጎዱ ወገኖች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ከማድረግ ባሻገር ኢትዮጵያ ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ የምታገኝባቸውን ቡናንና ሌሎች ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ በመጓጓዝ ትልቅ ድርሻ እንደተወጣ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዛሆ ዥዋን በበኩላቸው፤ ቻይና በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን በአጋርነት እየገነባች ነው። ይህም አንዱ አፍሪካን በመሠረተ ልማት በማስተሳሰር የበለጸገችና የተዋሀደች አፍሪካን ለመፍጠር ትልቅ አቅም ነው። ቻይና ከአፍሪካ ጋር በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማጠናከር ትፈልጋለች። ትናንት የተካሄደው የአምስት አመት የባቡር የሥራ ዘመን ክብረ በዓል ቻይና በቴክኖሎጂና በሌሎች ዘርፎች የእውቀት ሽግግር ስለማድረጓ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የጅቡቲ የመሠረተ ልማት ሚኒስትር ሀሰን ሆምድ ኢብራሂም፣ የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ሁለቱን አገሮች ከማስተሳሰር አልፎ ለቀጣናው ውህደት ቁልፍ ሚና አለው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኡመር ጌሌ በጋራ የኢትዮ ጅቡቲን ግንኙነት ለማሳደግ እየሠሩ ነው። ለዚህ ደግሞ ኮርፖሬሽኑ ትልቅ አቅም ነው። የንግድ ልውውጥና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በመፍጠር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

የምድር ባቡር አክሲዮን ማህበሩ በአምስተኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ላከናወናቸው ስኬታማ ሥራዎች አስተዋጽኦ ላደረጉ ባለድርሻ አካላት እውቅና ተሰጥቷቸዋል።



# ኢትዮ ቴሌኮም
## ለመዲናዋ የመንገድ ጽዳት ሴት ሠራተኞች ዘመናዊ የስልክ ቀፎ አበረከተ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም ዓለምአቀፉን የሴቶች ቀን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ጽዳት ሥራ ለተሰማሩ 353 ሴት ሠራተኞች ዘመናዊ የስልክ ቀፎ አበረከተ።

«የዲጂታል አካታችነት ለፆታ እኩልነት» በሚል መሪ ሃሳብ የተከበረውና ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው ዘመናዊ የስልክ ቀፎዎች በተበረከቱበት ወቅት የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ እንደተናገሩት፤ ሽልማቱ ሴቶች የዲጂታል ቴክኖሎጂ እና የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል እንዲሁም የዲጂታል ኢኮኖሚ ተካታችነትንና እኩልነትን ለማረጋገጥ ትልቅ ፋይዳ አለው።

የስልክ ቀፎዎቹ ተሸላሚ ሴቶች መደበኛ የቴሌኮም አገልግሎት ብቻ እንዲጠቀሙበት ሳይሆን ኢትዮቴሌኮም ተግባራዊ ያደረገውን የፋይናንስ አገልግሎት ጭምር እንዲጠቀሙበት የታሰበ እንደሆነ ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ተናግረዋል።

ወይዘሪት ፍሬህይወት እንደገለጹት፤ ከአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ጋር ስምምነት በማድረግ አዲስ አበባ ላይ ያሉ 400 ሺህ ሴቶችን ለማገዝ በቅርቡ ይፋ የሚደረጉ የተለያዩ ፕርግራሞች ተቀርጸዋል። በዋናነት ሴቶቹ በፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ እንዲሁም የዕለት ተዕለት የንግድ እንቅስቃሴያቸውን ሊያግዝ የሚችል የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት የዲጂታል ኢኮኖሚውን አካታች ማድረግን ያገናዘበ እንደሆነ ተናግረዋል።

በዕለቱ የዘመናዊ የስልክ ቀፎ ከተበረከተላቸው መካከል ወይዘሮ ምናሉ ክብረቴ እና ወይዘሮ አቦነሽ ፍቃዱ ሽልማቱ እንዳስደሰታቸው ገልጸው፤ ለተሰጣቸው እውቅና ኢትዮ ቴሌኮምን አመስግነዋል።

ኢትዮቴሌኮም ባለፉት ሦስት ዓመታት ሴቶችን ማካተትና ማብቃት የኩባንያው አንዱ እሴት አድርጎ በመያዝ ሴቶች የመረጃ እና የዲጂታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለመደገፍ 54 ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ ከ70 ሺህ በላይ የሞባይል ቀፎዎችን በገጠር አካባቢ ለሚገኙ ሴቶች ማበርከቱ ተገልጿል።

# ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ
## ራስ ገዝ ለመሆን ዝግጅት እያደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችለውን የዝግጅት ሥራ በማከናወን ላይ መሆኑን የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ። ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን እንደሚያሳድገው ተገልጿል።

የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጀማል የሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራስ ገዝ እንዲሆኑ የተጀመረውን ጥረት በማጠናከር ዩኒቨርሲቲው ዝግጅት እያከናወነ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ይረዳል ያሉት ዶክተር ጀማል፤ እንደ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ የመጀመሪያውን ሥራ ያደረግነው ራስ ገዝ ለመሆን ሁሉም እንዲቀበለው ሃሳቡን ማስረጽ ነው። በዚህ ረገድ የተለያዩ የውይይት መድረኮችና ዝግጅቶች ተካሂደዋል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር ጀማል ገለጻ፤ በራስ ገዝነት አስተዳደር ዙሪያ የአዕምሮ ዝግጁነት እንዲመጣ በተለያዩ መድረኮች ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሲሠራ ቆይቷል። በተለይም ሀሮማያ ከምስረታው ጀምሮ ከውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት ስላለው ራስ ገዝ ሲሆን እንዴት ሀብት ማሰባሰብ እንደሚችል እና በምን መልኩ ሥርዓቱን መምራት እንዳለበት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

ዩኒቨርሲቲው ያለውን የሰው አቅም በመገንባት፣ አስፈላጊ የትምህርት ግብዓቶችን በማሟላትና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ጀማል፤ የፋይናንስ አቅሙን በማጠናከር ሀብት የማመንጨት ሥራ ላይ ትኩረት ማድረጉን ጠቁመዋል።

በዩኒቨርሲቲዎች የተልዕኮ ልየታ መሠረት የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው አግባብ የራስ ገዝ ሆኖ መስራት እንዲችል የሚረዳ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን ዶክተር ጀማል አስታውቀዋል።

ዩኒቨርሲቲው በራሱ የንግድ ድርጅት አማካኝነት ገቢ ማመንጨት የሚያስችለው ግብረ ኃይል እና መመሪያ ማዘጋጀቱን ገልጸው፤ የተዘጋጀው መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ቦርዱ ከጸደቀው በኋላ እንደ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ራሱን ችሎ መዋዕለ ነዋዮቹን በማንቀሳቀስ፣ ከፍ ያሉ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ላይም በመሳተፍ ሀብት የሚያመነጭበት ሁኔታ ይመቻቻል ብለዋል።



ዶክተር ጀማል የሱፍ

በተለይም በከተሞች ኢንቨስትመንት ላይ በመሳተፍ፣ በግብርና፣ በሕክምና እና በተለያዩ ሴክተሮች ላይ ሀብት ለማመንጨት ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል።

የገቢ ምንጭን ከማስፋት ረገድ ዩኒቨርሲቲው ያሉትን የግብርና ሀብቶች በመጠቀም ምርቶችን በማሰባሰብ፣ ምርጥ ዘርን በማዘጋጀትና ተደራሽ በማድረግ፣ የዩኒቨርሲቲውን የጤና ማዕከል የሕክምና ቱሪዝም ማዕከል በማድረግ ረገድ ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር የሚያስችል ዕድል አለው ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር ጀማል እንዳሉት፤ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝነት በተለይም ጥራት ያለው ምርምር ለመሥራትና በሙያቸው ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ለማስመረቅ እንዲሁም በራሱ የፋይናንስ አቅም የተለያዩ ውሳኔዎችን ለመስጠት የተሻለ አቅም ይፈጥራል።

የማኅበረሰብ አገልግሎትን ከማስፋፋት አኳያ ዩኒቨርሲቲው ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ጀማል፤ በውጭ አገር ከሚኖሩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን የትብብር ምርምሮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነትን ከፍ ለማድረግ የሚረዳ እንደሆነም አመላክተዋል።

# ሴቶች በትምህርት ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶች ጥቃት ጥበቃ እና ምላሽ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ህሊና ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ የችሎታ እና ብቃት ማነስ ሳይኖርባቸው ባለው የግንዛቤ እጥረት ምክንያት ለሴቶች የትምህርት ዕድል ያለመስጠት ችግር በስፋት ይስተዋላል።

በተጨማሪ ያለዕድሜ ጋብቻና ከጤና ጋር በተያያዙ በርካታ ችግሮች ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ከሚያግዱ ምክንያቶች መካከል ናቸው። ችግሮቹን ለመቅረፍና ሴቶችን ከትምህርት የሚገድቡ ጉዳዮችን ለማላቀቅ የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

የዘንድሮ የሴቶች ቀን በአገራችን «እኔ የእህቴ ጠባቂ ነኝ» በሚል መሪ ቃል ለ47ኛ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ112ኛ ጊዜ የሚከበር ሲሆን፤ ዕለቱን በማስመልከት በርካታ የንቅናቄ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

የሴቶች ቀን መከበሩ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለመቀነስና የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዳ የተቀናጀ ሥራ ለማከናወን ይረዳል ሲሉ ወይዘሮ ህሊና ተናግረዋል።

ሴቶች በጾታቸው ምክንያት በርካታ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንዲሁም ፖለቲካ ተጽእኖዎች ይደርስ ባቸዋል፡፡ ይህን ተጽእኖ በመቀነስ ረገድ የወንዶች ሚና ጉልህ በመሆኑ ለሴቶች እኩል የትምህርት፣ የሥራ ዕድል፣ የጤና ተሳታፊነት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ጥሪ መቅረቡን አስታውቀዋል።

ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የሴቶችን መብት እንዲከበርና ተጠቃሚነታቸው እንዲጎለብት ለማድረግ በተለያዩ ክልሎች ስልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን እያዘጋጀ ይገኛል። በተጨማሪ ሴቶች በኅብረት ሥራ እንዲደራጁና የብድር እና ቁጠባ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማመቻቸት በኢኮኖሚ የተሻሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሠራል ሲሉም ተናግረዋል።

ሴቶች በጾታቸው ምክንያት የሚደርሱባቸውን ጫናዎች እንዲሻገሩ በቅድሚያ ስብዕና ግንባታቸው ላይ ያተኮረ ሥራ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ቤተሰብ ወሳኝነት አለው። በመሆኑም ማህበረሰቡን በሴቶች እኩልነት ላይ ያለውን ግንዛቤ ከማሳደግ ባለፈ ሴቶች የራሳቸውን አቅም እንዲያጎለብቱ የሚረዱ የሕይወት ክህሎት ስልጠናዎች እየተሰጡ መሆኑን ገልጸዋል።

የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በተከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዓል ላይ አገር በቀል የሥራ ፈጠራ ውጤቶች ለሴቶች ኢኮኖሚያዊ ብቃት፣ ፈጠራንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን እናረጋገጥ፣ ሁለንተናዊ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለሰብዓዊ መብት መከበር የሚሉ ሃሳቦችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በተለያዩ ክልሎችና ዞኖች ላይ መሰራቱን ወይዘሮ ህሊና ጠቁመዋል።

# «በሴቶች ላይ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የማንቂያ ደወላችን ነው ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

የሴቶች አጀንዳ የሕዝብ ጉዳይ እንዲሆን የሚሠራ፣ መፍትሔ የሚያፈላልግ፣ በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ እውቀትና ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ለዚህ ዓላማ የሚያስተባብር ጠንካራ ማህበር ያስፈልገናል ሲሉም ገልጸዋል።

ለሴቶች ተስፋ ሰጪ አርዓያ የምትሆናቸው ሴት ነች። በግለሰብ ደረጃ ድምጻቸውን አጥፍተው ወገን የሚረዱ፣ ተስፋ ሰጪ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ሴቶች ላይ መብራት እናብራባቸው፣ እውቅና እንስጣቸው፣ እናክብራቸው ብለዋል።

ፕሬዚዳንቷ እንዳስታወቁት፤ በውጭ ርዳታ ላይ የተንጠለጠሉ ሥራዎች ዘላቂነታቸው አስተማማኝ አይሆንምና የተለመደውን አካሄድ በመከተል በትንንሽ ስኬቶች ሥራው ተጠናቀቀ ተብሎ የሚተው ከሆነ ለውጥ ሊመጣ አይችልም። ስለሆነም መፍትሄዎችን በአዲስ ሀሳብና አካሄድ መቃኘት ያስፈልጋል።

በተጨማሪ ከአፍሪካ አገራት ጋር ያለንን ትስስር ለማጠናከር ከአራት ዓመት በፊት የተመሠረተው «የአፍሪካ ሴት መሪዎች ጥምረት» /AWLN/ የኢትዮጵያ ቅርንጫፍን ማጠናከርና የልምድ ልውውጦችን ማጎልበት እንደሚገባ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ አስታውቀዋል።

# «ኢትዮጵያ ብዙና አመቺ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሲሠራ ቆይቷል ነው ያሉት፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ባደረጉት ቆይታ ግሊትዝ ፋርማሲን በኢትዮጵያ ለመክፈት እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ቻውዳርይ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከመድኃኒት ዘርፉ በተጨማሪ ኢንቨስት ሊደረግባቸው የሚችሉ እንደግብርና፣ ጨርቃጨርቅ እና ሌሎች ብዙ ያልተሠራባቸው ዘርፎች አሏት፡፡

በኢንቨስትመንት ዙሪያ ብዙ መሰራት ይችላል የሚሉት ቻውዳርይ ኢትዮጵያ ያላት የሰው ኃይል እንዲሁም እንግዳ ተቀባይነቷ በዓለም ላይ ያሉ ኢንቨስተሮች ዓይናቸውን እንዲጥሉባት ያደርጋል ብለዋል፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቴ በፊት ስለ ኢትዮጵያ የተሳሳተ አመለካከት ነበረኝ ያሉት ቻውዳርይ ስመጣም የሰማሁት ነገር ውሸትና ስህተት እንደነበርና ኢትዮጵያ ሰላማዊና ለኢንቨስትመንት የምትመች አገር መሆኗን አረጋግጫለሁ ብለዋል፡፡ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙና ኢንቨስት እንዲደርጉ እንደሚያበረታቱ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው የጉብኝቱ ተሳታፊ የናቢቃሲብ ኢንዱስትሪ አመራር ሀሲብ ናሲር ኢትየጵያ ከሌሎች አፍሪካ አገራት በተለየ ለኢንቨስትመንት የምትመች አገር መሆኗን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለውጭ ኢንቨስተሮች የሰጠችው ትኩረትና ያላት ፖሊሲ፤ ኢንቨስትመንቱን ለመቀላቀል የሚመች እና ወደ ሥራ እንድንገባ የሚያበረታታ ነው ብለዋል፡፡

ከሌሎች አገራት በተሻለ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢዝነስ ለመጀመር የሚያስችሉ ብዙ አማራጮች አሉ ለዚህም ከምሥራቅ አፍሪካ ትልቁ መድኃኒት አቅራቢ የሆነው ተቋማቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ እንደሚጀምር ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የፓኪስታን አምባሳደር ሾዛብ አባስ፤ በኢትዮጵያ ጉብኝት ያደረጉት የፓኪስታን ኢንቨስተሮች ከተለያዩ ዘርፎች የመጡ መሆናቸው ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

ኢትጵያና ፓኪስታን በግብርና ዘርፍ በስፋት የሚሠሩ አገራት በመሆናቸው በግብርና ዘርፉ ላይ የሚኖራቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ይረዳል ያሉት አምባሳደሩ የፓኪስታን ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ መጥተው ውይይት ማድረጋቸን በመረጡት የኢንቨስትመንት አማራጭ እንዲሰማሩ የሚያነቃቃ ነው፡፡ የሁለቱን አገራት የገበያ ትስስርም ይበልጥ የሚያጠናክር ይሆናል ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትኩረት ለዋጋ ንረቱ እና የኑሮ ውድነቱ!

በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ከሚከሰቱ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የኑሮ ውድነት ነው። ይህንን ችግር ለመፍታትም የንግዱ ማኅበረሰብ በተለይም መንግስት በከፍተኛ ኃላፊነት እንዲንቀሳቀሱ ይጠበቃል።

በአገራችንም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለውጡን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተኑ ከሚገኙ መሰረታዊ ችግሮች መካከል አንዱ የኑሮ ውድነት ነው፤ የኑሮ ውድነቱ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች የተከሰቱ ቢሆኑም፤ በአብዛኛው ችግሮቹ ሰው ሰራሽ የመሆናቸው እውነታ የሕዝብን ኑሮ የመገዳደር አቅሙ ዕለት ተዕለት እያደገ እንዲመጣ አድርጎታል።

በአንድ በኩል በአገር አቀፍ ደረጃ ያለው የገበያ ስርአት የተበላሸ መሆን፤ በሌላ በኩል ስርአቱን አስተካክሎ ለመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው መንግስታዊ ተቋማትና ቢሮዎች በችግሩ ላይ የማያዳግም እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ በተለመዱ ምክንያቶች ራሳቸውን አጥረው መገኘታቸው ለችግሮቹ መገንገን አይነተኛ ምክንያት ሆኗል።

እንዲያውም የሚመለከታቸው ተቋማት ሁሌም ለችግሮቹ እንደ ምክንያት የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች የተለመዱና ሁሌም ችግሩ ከገበያ ሰንሰለት ጋር ይያያዛል የሚል መሆኑ ሲታይ ሕዝብን ከማሰልቸት አልፎ ተስፋ ወደመቁረጥ እያደረሰው ይገኛል፡፡ ይህም የንግድ ስርዓቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለባቸውን ተቋማት ችግሮችን የመፍታት አቅምና ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እየከተተው ነው።

አሁን ላይ ከገጠር እስከ ከተማ አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶች የሚፈጠሩ የተጋነኑ የዋጋ ንረቶች በተለይም በከተሞች አካባቢ በሚኖሩ ዜጎች ላይ እያስከተሉት ያለው መጠነ ሰፊ ችግር በዚሁ ከቀጠለ፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች በልቶ የማደር ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል መገመት የሚከብድ አይሆንም።

በአገሪቱ ካለው ተጨባጭ እውነታ አንጻር በአሁኑ ወቅት የዋጋ ጭማሪ ያልተደረገባቸው ለገበያ የሚቀርቡ ሸቀጦች አሉ ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ጠዋት የገዙትን ሸቀጥ ማታ በተመሳሳይ ዋጋ ማግኘት በአብዛኛው የሚታሰብ አይደለም፤ ማታ የገዙትን እንዲሁ ጠዋት በነበረበት ዋጋ አያገኙትም። ከዚህም የተነሳ የሸቀጦች ዋጋ ከቁጥጥር ውጪ የሚሆንበት ስጋት ዕለት ተዕለት እየጨመረ ነው ።

የቀደሙትን ትተን በቅርቡ እንኳን በጤፍ ዋጋ ላይ በአዲስ አበባ እየታየ ያለው ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ /በኩንታል ከሁለት ሺህ ብር በላይ/ መካከለኛ ገቢ ባለው ኅብረተሰብ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የመንግስት ሰራተኞችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ሁለንተናዊ ተጽእኖ በቀላሉ የሚሰላና በዝምታ ሊታለፍ የሚችል አይደለም።

ለግብርና በተሰጠ ትኩረት በአገሪቱ ከፍተኛ ምርት በተገኘበት ወቅት የብዙ ኢትዮጵያውያን የምግብ ምንጭ በሆነው ጤፍ ላይ የዚህን ያህል የዋጋ ጭማሪ መታየቱ በምንም ዓይነት መልኩ በተለመዱ ምክንያቶቹ አለባብሰው ሊያልፉት የሚችሉት ጉዳይ አይሆንም።

የምርት እጥረት በሌለበት ወቅት የተፈጠረው ይህን መሰል የዋጋ ንረት፤ በመንግስት በኩል ከፍያለ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ ችግሩ ሕዝብን ለምሬት የሚዳርግና የመኖር ህልውናውን በእጅጉ የሚፈታተን በመሆኑ በተለይም በንግድ ሰርዓቱ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማት ችግሩን ከፍ ባለ ደረጃ ሊመለከቱትና የማያዳግም መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ ሊቀይሱ ይገባል።

በደላላና በቆየ የተበላሸ የገበያ ስርአት እየተመካኘ መፍትሄ አልባ ሆኖ የዘለቀው ይህ ችግር፤ በቂ የትርክት እና የምሬት ጊዜዎችን አልፏል፡፡ ከእንግዲህ እነዚህን ችግሮች እንደምክንያት አድርጎ ማምጣት የሞራል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን ጨምሮ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በህግ ከተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት አንጻር ራሳቸውን በአግባቡ በመገምገም፤ እንደ አገር ችግሮቹን ተሻግሮ መጓዝ የሚቻልበትን ሁለንተናዊ ቁመና መፍጠር ይኖርባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ከተለመዱ ምላሾችና ዝምታዎች ወጥተው ስትራቴጂክ በሆነ መንገድና በተቀናጀ እና በተናበበ አካሄድ ዜጎች ባልተገቡ ምክንያቶች የሚከፍሉትን ዋጋ ማስቆም ይኖርባቸዋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትውልዶች የዘመን ሥሪት

(በጌታቸው በለጠ/ዳግላስ ጴጥሮስ)

**የመነሻ ወግ፤**

"የአንድ ትውልድ የዘመን ስሌት ምን ያህል ነው? መለያ ድንበሩስ" - ጠያቂዎችንና መላሾቹን ሊያግባባ ያልቻለ የዓለማችን ምሁራን የጋራ ጥያቄ ነው። ሞጋቹ ጥያቄ ምላሽ የተነፈገው በዛሬ ጀንበር ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም እየተጠየቀ መሰንበቱ ስለማይቀር፤ ጊዜው ደርሶ ቁርጥ ያለ መልስ እስከናገኝ ድረስ "አጉራህ ጠናኝ" በማለት "የእንደመሰለን ሃሳባችንን" እያነሳሳን መወያየቱን እንቀጥልበታለን።

እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ዘመን ይሠራል፤ በራሱም ዘመን የራሱን አሻራ አትሞ ያልፋል። ይህ እውነታ በሁሉም ያገባኛ ባይ የእውቀት ዘርፍ ተዋንያን ዘንድ አሜንታን ያተረፈ ስለሆነ እጅግም ለክርክር በር አይከፍትም። "ትውልድ በራሱ ዘመን ይሰለጥናል ወይንም ካስፈለገ ይሰየጥናል"። ይህ ማለት ግን አዲስ መጭው ትውልድ መንበሩን የሚቆጣጠረው ከባዶ ተነስቶ ሳይሆን በነባር ትውልዶች መሠረት ላይ የራሱን ጡብ እያስቀመጠ መሆኑም አይዘነጋም።

የግብጾች የቤተሰባዊ ትውልድ ቅብብሎሽ ተሞክሮ በአብነት ቢነሳ ይጠቅም ስለመሰለን ምሳሌነቱን ለማሳያነት እንጠቀምበት። ሌሎች ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው አገራትም ሊኖሩ እንደሚችሉ ልብ ይሏል። ግብጾች ለቤተሰብ መኖሪያ የድርብ (ፎቅ) ሕንጻዎችን ወደ ላይ ሲያንጹ ለቀጣዩ ትውልድም የድርሻውን እየተውለት ነው። ለምሳሌ፡- ወላጆች የታችኛውን የምድር ቤት ወለል ለራሳቸው ሲሰሩ በቀጣዮቹ ወለሎች ላይ ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው የራሳቸውን መኖሪያ ቤት እንዲገነቡ ጭምር ኮንክሪቱንና ቀጣዩ ወለል የሚያያዝበትን መቀጠያ ብረት ጫፉን አዘጋጅተው ይተውታል።

እነዚህ ብልህ የግብጽ ሰዎች ይህንን የሚያደርጉት ነባሩና መጻኢው የቤተሰብ አባላት የጋራ ሕንጻ እንዲጋሩ ስለፈለጉ ብቻ ሳይሆን ቤተሰባዊ ቁርኝቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲቀጥል ስለሚፈልጉም ጭምር ነው። ይህ ቤተሰባዊ ትሥሥራቸው ለኅብረተሰባቸው ጥንካሬ የዘመናት ተሞክሮ ስለሆነ ዛሬም ባህሉ አልደበዘዘም። ይህ ጸሐፊ በቦታው ተገኝቶ ተሞክሯቸውን ተሞክሮ ትምህርት ቀስሟል።

የትውልድ ሰንሰለት ሳይበጠስ ሊቀጥል የሚችለው ከላይ እንደተጠቀሰው ምሳሌ በቤተሰባዊ መስተጋብር ብቻ ሳይሆን በጋራ አገራዊ ጉዳዮችም መቀባባል፣ መደጋገፍ፣ መከባበር፣ መረዳዳትና መደናነቅ ሲቻልና ሲሰራበት እንጂ ከሥር የተሸከመውን የትናንት መሠረት በማናጋትና ምሰሶውን ለመንቀል በመታገል ሊሆን አይገባም።

እርግጥ ነው ትውልዶች የታነጹባቸው የሥር መሠረቶችና ታሪኮች በሙሉ ሁሉም እንደሚፈልገውና እንደሚመኘው የሰመረና የተዋበ ላይሆን ይችላል። የኋለኛው መሠረት አንዳንዴ ስንጥቅም ሆነ ክፍተት ሊኖርበት ይችል ይሆናል። ቢሆንም ግን ተቃውሞን ለመግለጽ በመፈለግ ብቻ የታችኛውን መሠረት ሙሉ ለሙሉ በመናድ ሽቅብ የተንጠለጠሉበት ምሰሶ ብቻውን እንዲቆም መሞከር ትርፉ ተያይዞ መውደቅን ማስከተሉ አይቀርም።

የነገረ ትውልድ የወግ መንደርደሪያችን ይህንን ያህል ለመነሻ ሃሳባችን ጉዝጓዝ ከሆነን ዘንድ ወደ አገራዊ ጉዳያችን ቅኝት ከማለፋችን አስቀድሞ ዓይን ከፋች የሆነ አንድ የአሜሪካኖችን "ትውልድ ነክ" ጥናት ለመደላድል እንዲረዳን ዘርዘር አድርገን እንመልከት። "ብልህ ሰው ከሌሎች እውቀትን ይሸምታል፤ ከራስ ድካም አሸናፊነት ይማራል" እንዲሉ መሆኑን ልብ ይሏል።

"የአያት ቅድመ አያቶቻችን የሩጫ ፍጥነት ቀጣዩን ትወልድ ተረጋግቶ እንዲራመድ ረድቶታል።" ይህ ድንቅ አባባል በብዙ ሕዝቦች ቋንቋዎች ውስጥ ይነገራል። የአባባሉ ሁለተኛው ክፍልም እንዲህ ይላል፡- "በፈጣን ሩጫዎቻቸው መካከል ከስህተት ነፃ እንዳልሆኑም ስለምናምን ጥፋታቸውን በአክብሮት፣ በጥበብና በተሻለ ተግባር ለማረም እንሞክራለን እንጂ አጽማቸውን ቀስቅሰን ይግባኝ በማይባልበት የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አቁመን የዳግመኛ ሞት ፍርድ እንዲፈረድባቸው አንጨክንም " ድንቅ ብሂል ነው።

በአመራር ጥበብና በኮሚዩኒኬሽን የእውቀት ዘርፍ በአሰልጣኝነታቸው፣ በአስተማሪነታቸውና በተጠቀሱት ሁለት ዲሲፕሊኖች ላይ በጻፏቸው መጻሕፍት የሚታወቁት ጆን ካልቪን ማክስዌልና አራት የሥራ ባልደረቦቻቸው በቨርቹዋል ቴክኖሎጂ አማካይነት የሰጡትን ድንቅ ሥልጠና ይህ አምደኛ ለመከታተል እድል ገጥሞት ነበር። ዘመን ወለዱን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከእነዚህ የዓለማችን ጉምቱና በሳል ምሁራን ጋር በማገናኘት ትምህርት እውቀት እንድንቀስም መድረኩን ያመቻቹት የራይዝ ኤንድ ሻይን ኢንተርናሽናል ተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወዳጄ ዶ/ር ዳንኤል ጣሰው ነበሩ። ልባዊ ምሥጋናችን ይድረሳቸው።

ከማክስዌል ባልደረቦች መካከል ፓትሪክ ሌንሲዎኒ የተባሉት ምሁር በራሳቸው የሥልጠና ክፍለ ጊዜ ያስተማሩት የአገራቸውን የአሜሪካንን የቅርብ ዘመናት የትውልዶች የዘመን ሥሪት አወቃቀር ከፈጠራ፣ ከሥራ ባህልና ከበርካታ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎች አንጻር በምሳሌነት በመተንተን ነበር። ትምህርቱንም በራሳችን ዐውድ የአገራችንን የትውልድ ፍሰት እንድንፈትሽ አበረታተውናል።

ፓትሪክ ለመሸፈን የሞከሩት እ.ኤ.አ ከ1925 እስከ 2020 ያሉትን የዘጠና አምስት ዓመታት የአሜሪካዊውን ትውልዶች በአምስት ዘመናት በመከፋፈል ነበር። ከ1925 እስከ 1946 የነበረው ትውልድ የተሰየመው ለአገር ግንባታ የጨከነና የለሆሳስ ትውልድ (Builders/Silent Generation) እንደነበረ ገልጸው ብዙ ከመፎከር ይልቅ ለአገሩ ብዙ መሥራት የትውልዱ ዋና መገለጫ መሆኑን አስረግጠው ተናግረዋል። ለባህሉና ለሥርዓቱም "ወግ አጥባቂ" ተብሎ የሚፈረጅ ዓይነት ሲሆን ለሥራና ለፈጠራ የነበረው ተነሳሽነትም በዋነኛነት መሠረታዊ ቁሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት ይተጋ እንደነበርም በዝርዝር አመላክተዋል።

በሁለተኝነት የጠቀሱት ትውልድ ከ1946 እስከ 1964 ዓመታት የኖረውንና የመታወቂያና የመለያ ስያሜውም እንደ "እንጉዳይ የፈላ ትውልድ" (Baby Boomers) የሚባል ነበር። ይህ ትውልድ ይህንን ስያሜ ሊያገኝ የቻለው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የውልደት መጠኑ (Birth Rate) በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ብዙ ሕጻናት (እስከ 78 ሚሊዮን ይገመታሉ) በአሜሪካ ምድር ብቻ መወለዳቸውን ለመግለጽ ነው።

የትውልዱ ባህርይ የተገለጸውም "የተሻለው ሁሉ የሚገባው ለእኔ ነው" ባይ ተድርጎ ነው። በዚህ ትውልድ ዘመን የከለር ቴሌቪዥን የተዋወቀበት፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መነቃቃት የተስተዋለበት፣ ወደ ጨረቃ ጉዞ ዝግጅት የተጧጧፈበት፣ አሜሪካ ከቬትናም ጋር ጦርነት ውስጥ የገባችበት፣ የክሬዲት ካርድ በስፋት የሁሉም ሰው መገልገያ መሆን የጀመረበት፣ ኤልቪስ ፕሪስሊን የመሳሰሉ የሙዚቃ ከዋክብት የደመቁበት፣ ቢትልስና ሮሊንግ ስቶን የተሰኙ ባንዶች የገነኑበት ትውልዱም አብሮ ማበድ የጀመረበት ዘመን ነበር። በትውልዱ ዘንድ ከኢንዱስትሪ ምርቶች ይልቅ በዋነኛነት አገልግሎቶች (Services) ተመራጭ ነበሩ።

ሦስተኛው ትውልድ ጄኔሬሽን X (Generation X or Busters) በመባል የሚታወቅ ሲሆን የሚሸፍነው ዘመንም ከ1965 እስከ 1982 ያሉትን አስራ ሰባት ዓመታት ነው። ይህ ዘመን በራሷ በአሜሪካ ውስጥም ሆነ በሌላው የዓለም ክፍል ታላላቅ የሚባሉ ክስተቶች የተስተዋሉበት ዘመን ነበር። ኒል አርምስትሮንግ በአፖሎ 11 ጨረቃ ላይ ያረፈው፣ ቻሌንጀር የተባለችው መንኮራኩር አየር ላይ ጋይታ የተሳቀቁበት፣ አገራቸው በቬትናም ጦርነት የሽንፈት ዋንጫ የጨለጠችበት፣ የሃሊ ኮሜት ኮከብ ተከስታ ዓለም የተደመመበት፣ የስቶክ ገበያ አደጋ ላይ የወደቀበት፣ የቴሌቪዥን የመዝናኛ ቻናሎች እንደ አሸን የፈሉበት፣ ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመንን የለየው የበርሊን ግንብ የፈረሰበት ወዘተ. ዓመታት ነበሩ። የሥራ ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ የተነቃቃበትና የባለሙያዎች የሥራና የዕውቀት ልምድ ከበሬታ ያገኘበት ዘመንም ነበር።

አራተኛው ትውልድ የእሥራ ምዕቱ ትውልድ (Millennias/Generation Y) በመባል የሚታወቅ ሲሆን የሚሸፍነው ዘመንም ከ1983 እስከ 2000 ያሉትን ዓመታት ነው። ይህ ትውልድ የሥራና የሕይወት ፍልስፍናው ትራንስፎርሜሽን (ሥር ነቀል ለውጥ) የሚል ሲሆን "ሕይወትን በካፌቴሪያ እንደምናገኘው አገልግሎት ያህል አቅልለን ማየት ይኖርብናል" የሚል

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የትውልዶች የዘመን ...

ከገጽ 5 የዞረ

ፍልስፍና የነበረው ትውልድ ነበር።

በእነዚህ የዓመታት ክልል ውስጥ ዓለም አዲሱን የእሥራ ምዕት (ሚሊኒዬም) በዓል በስጋትና በተስፋ ያከበረችበት፣ አሸባሪነት ለአሜሪካ ከፍተኛ ስጋት የሆነበት፣ ትውልዱም ከፍርሃትና ከውጥረት ለመላቀቅ ልዩ ልዩ የመዝናኛ ፊልሞችን በመመልከት የተጠመደበት፣ የክሬዲትና የዱቤ የንግድ ልውውጦች የእያንዳንዱን ዜጋ ሕይወት የተቆጣጠሩበት ዘመን ነበር።

አምስተኛውና የመጨረሻው ዘመን "የX" ትውልድ (Generation X) በመባል ሲታወቅ የሚሸፍነውም ከ2001 እስከ 2015 ያሉትን ዓመታት ነው። የዚህ ትውልድ ዋነኛ መገለጫ በቴክኖሎጂ ፈጠራ መራቀቅ የጀመረበትና የማሕበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚነቱን እንደ ጣኦት ያመለከበት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ ሕይወቱን ማቆራኘት የጀመረበት ዘመን ነበር። በአሜሪካም ሆነ በሌሎች አገራት ልዩ ልዩ አሉታዊና አወንታዊ ክስተቶች መስተዋላቸውም አልቀረም።

ለምሳሌ፡- አሜሪካ አፍጋኒስታንን መውረሯ፣ አብዛኞቹ የእስያ አገራት በሱናሚ አውሎ ነፋስ የደቀቁበት፣ የየአገራቱ ምሥጢሮችና ጠንከር ያሉ የውስጥ ገመናዎች በዊኪ ሊክስ (Wiki Leaks) የመረጃ መረብ እያፈተለኩ በግላጭ አደባባይ የተነዙበት፣ የተራቀቁ የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች (3D Movies, Smart TV) የመሳሰሉ የተዋወቁበት፣ ወጣቱ ክሬዲት ካርዱን ለአልባሌ ጉዳዮች እየተጠቀመ ራሱን በዱቤ እዳ ውስጥ የዘፈቀበት፣ የተቦጫጨቀ ጂንስ በመልበስ የሥልጣኔና የፋሽን ምልክት አድርጎ እንዲቆጠርለት ያስተዋወቀበት ዘመን ነበር።

**የእኛስ ትውልዶች?፤**

የአገሬን ቀዳሚ ትውልዶች በተመለከተ በተለየ ሁኔታ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከሥራ ባህል፣ ከሕይወት መርህ ፍልስፍና፣ ከዕውቀት ጎሣሣ ትጋት፣ ከአኗኗር ዘይቤ፣ ከሥርዓተ መንግሥታትና የአገዛዝ ዘይቤና ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አንጻር እየተነተኑ የሚያሳዩ ጥናቶችን ይህ ጸሐፊ ተሰንዶ ስለማንበቡ እርግጠኛ አይደለም። ጥናቶች ተሰርተው ከሆነም በግላጭ ቀርበው ውይይት ሲደረግባቸው እጅግም አይስተዋልም። አልፎ አልፎ መነካካታቸውን መካድ ግን አይቻልም።

የራስን የመዋጮ ጠጠር መወርወሩ መልካም መስሎ ስለታየኝም "በወፍ በረር ቅኝት" እንዲሉ ለውይይት መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ግርድፍና ከዚህም ከዚያም የተቃረሙ ምልከታዎችን ከንባቤ፣ ከታላላቆች ያደመጥኩትን፣ በግሌም የዐይን እማኝ የሆንኩባቸውን ልምድና እውቀቶች በማሰባሰብ የአገሬን የትውልድ ፍሰት በተመለከተ እነሆ የድኅረ ኢጣሊያ ወረራን (1934 ዓ.ም) ማግሥት መነሻ በማድረግ እስከ 2014 ዓ.ም ያሉትን ስምንት አሥርት ዓመታት እንደሚከተለው "በአምስት የትውልድ ዘመናት ከፋፍዬ" የጥናት መነሻ ቅኝት ለማድረግ ሞክሬያለሁ። ይህ የጸሐፊው የግሉ ምልከታ መሆኑንም ቀድሜ አሳውቃለሁ።

**የመጀመሪያው ትውልድ፡-** ከ1934 እስከ 1953 ዓ.ም ያለውን የአገር ገንቢዎች ትውልድ (Nation Builders) ይሸፍናል። ይህ ዘመን አገሪቱ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በአሸናፊነት የተወጣችበት፣ የተለያዩ የድል ማግሥት የሙብት ጥያቄዎችና የይገባናል ሙግቶች በዋናዎቹ አርበኞች፣ በስደተኞች፣ በውስጥ አርበኞችና በባንዳዎች መካከል የተፋፋመበት፣ በወረራው ምክንያት መንግሥታዊ ሥርዓቱ ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ የፈራረሰበትና የተሰነጣጠቀበት ዘመን ነበር።

የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ለመወሰን በተለይም በትምህርቱ ዘርፍ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ግብግብ የፈጠሩበት፣ ኢትዮጵያ በኮሪያና በኮንጎ ጦርነቶች የተሳተፈችበት፣ ወጣቱ ትውልድ አገሩን ለመገንባት ቁርጠኝነት ያሳየበት፣ ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገራት የተላኩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በጨረሱ ማግሥት አገራቸውን ለማገልገል እየተጣደፉ የመጡበትና መንግሥት በሚመድባቸው የትኞቹም የሥራ መስኮች ሳያመነቱ ለማገልገል የጨከኑበት ዘመን ነበር።

የኢጣሊያ ወራሪዎች ተክለዋቸው የሄዱት አንዳንድ አይረቤ ልምምዶች ሥር መስደድ የጀመሩበት፣ አገሪቱ በዋነኛነት ለትምህርትና ለግብርና ትኩረት የሰጠችበት፣ ፊውዳላዊው የመሬት ቅርምት የተጧጧፈበት፣ የውጭ ዲፕሎማሲው በአንጻራዊ መልኩ በተሻለ አቋም የተጠናከረበት፣ የንግዱ ዘርፍ በዋነኛነት በውጭ አገራት ዜጎች የተያዘበት፣ በወታደራዊ ክፍሎች መካከል መቆራቆስ በግልጥ የተስተዋለበትና በክብር ዘበኛው ጀኔራል በመንግሥቱ ነዋይና በወንድማቸው ግርማሜ ነዋይ ፊት ቀደምትነት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደርጎ የከሸፈበት ወቅት ነበር። ይህ ጸሐፊ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከሦስት አሥርት ተኩል ዓመታት በፊት የሠራው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ ዝርዝር ጉዳዮችን በስፋት ዳሷል።

**ሁለተኛውን የትውልድ ዘመን** "የነውጠኛው ትውልድ ዘመን" (Revo Generation) ብዬ ሰይሜዋለሁ። ዘመኑም ከ1954 እስከ 1966 ያሉትን ያጠቃልላል። ትውልዱ ትምህርትና ለውጥን እኩል ያፈቅር የነበረበት፣ ከቅኝ ግዛት ከተላቀቁ የተለያዩ የአፍሪካ አገራት በስኮላር ሺፕ የመጡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን "የመሬት ላራሹን" ትግል በአብሮነት የደገፉበት፣ በእውቀታቸው፣ በንባብ ችሎታቸውና በድርሰት ሥራዎቻቸው ከፍታ ላይ የነበሩ ወጣቶች የታዩበት፣ ብሔረተኛ የፖለቲካ ቡድኖች ያቆጠቆጡበት፣ ኢኮኖሚው የተሻለ መነቃቃት ያሳየበት፣ ወታደራዊ መዋቅሩ የተጠናከረበት፣ የድርቅና የርሃብ በላ የተከሰተበት፣ የንጉሡ ነገሥቱ ዙፋን በከፍተኛ ሁኔታ መነቃነቅ የታየበትና የሕዝብ አመጽ ከቁጥጥር በላይ የወጣበት የጋለ የትውልዱ አብዮታዊ ዘመን ነበር።

**ሦስተኛው ትውልድ፡-** የወታደራዊ አገዛዝ ዘመን (ከ1967 እስከ 1983 ዓ.ም) ትውልድ ሲሆን "የጠፋ ትውልድ" (Lost Generation) ቢባል ተገቢ ስያሜ ይመስለናል። ወታደራዊው ደርግ የንጉሡን ዙፋን የገለበጠበትና ንጉሡን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች በገፍ የተጨፈጨፉበት። "ሶሻሊዝም" የፖለቲካው መርህ መሆኑ፣ የእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ትግበራ፣ የገጠር መሬት አዋጅ፣ የከተማ ትርፍ ቦታና ቤት መውረስ፣ የኢንዱስትሪዎች ወደ መንግሥት ንብረትነት መዛወር፣ እለት በእለት በአዋጆችና መመሪዎች እንደጎርፍ መጥለቅለቅ የታየበት።

የቀይና የነጭ ሽብሮች ፍጅት፣ ድርቅና ርሃብ፣ የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት መዘርጋት፣ የሱማሊያ ጦርነት በድል መቋጨት፣ "ከገንጣይ አስገንጣይ" ቡድኖች ጋር የማያባራ ጦርነት፣ ለጦርነት የወጣቶች አፈሳ መጧጧፍ፣ የኢሠፓ መመሥረትና የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ ዓለም አቀፉ የሶሻሊስት ሥርዓት መፈራረስ፣ የደርግ መንግስት መሰነጣጠቅና መፈረካከስ ከብዙ ክስተቶች መካከል ጥቂቶቹና የትውልዱን ዘመን የሚወክሉ ናቸው። "ወዛደራዊ አምባገነንነት" የዘመኑ ዋነኛ የፍልስፍና መንፈስ ነበር።

**አራተኛው ትውልድ፡-** ከ1984 እስከ 1997 ዓ.ም ያሉትን ዓመታት ይወክላል። የትውልዱን ዘመን "የግፈኞች ሰለባ" (The Victimized Generation) ብለን ልንሰይመው እንችላለን። የበረኸኞቹ ጦረኞች ሥልጣን ተቆጣጥረው በትውልዱ ዘመን ላይ የፋነኑበት፣ ዘርና ብሔር ተበታትኖ በየመደቡና በየጓዳው እንደ ችግኝ የፈላበት፣ የፖለቲካ ቡድኖች እንደ እንጉዳይ ያበቡበት፣ "ነፃ" በሚል ስያሜ የህትመት ውጤቶች እንደ መና የዘነቡበት፣ አድሎና ዘረኝነት ጥግ የደረሰበት፣ ዘረፋ፣ የአየር በአየርና የኮንትሮባንድ ንግድ የተስፋፋበት ዘመን ነበር።

የህብት ሽሚያ ወደ ባህል ደረጃ ያደገበት፣ የልማት ጅምሮች እዚህም እዚያም የሚስተዋሉበት፣ የእውቀት መስፋፋት ሳይሆን የተዝረከረከ የትምህርት ተቋማት ግንባታ የተስተዋለበት፣ ከኤርትራ ጋር የጦርነት ፍልሚያ የተደረገበት፣ "አንጻራዊ" የሃይማኖት ነፃነት የታየበት፣ የወረቀት ገንዘብ ለውጥ የተደረገበት፣ የሰብዓዊ ሙብት በአደባባይ እየተጣሰ መከራና ግፍ የናኘበት፣ አገራዊ አንድነት አደጋ ላይ የወደቀበትና አምባገነንነት የደመቀበት ዘመን ነበር። ወጣቶች ሥርዓቱን ለመለወጥ ከፍተኛ ትግል ለማድረግ የጨከኑበት፣ ኢህአዴጋዊ ፖለቲካና የሀብት ቅርምት የተጣመሩበት ዘመንም ነበር።

**አምስተኛው ትውልድ (?)፡-** ከ1998 እስከ 2014 ያለውን ዘመን የሚወክል ሲሆን ግራ ገብ ትውልድ (Confused Generation) በማለት ሰይሜዋለሁ። ከ97 ምርጫ በኋላ ፖለቲካውንና ሥርዓተ መንግሥቱን በዋነኛነት የሚመራው የሕወሓት ቡድን ከውስጥና ከውጭ የውጥር ተይዞ የሚይዝ የሚጨብጠው የጠፋበት። የጋዜጠኝነት ዋጋ የረከሰበትና ብዙ ባለሙያዎችም የተሰደዱበት፣ መንግሥታዊ እልህና እብሪት በግላጭ የተስተዋሉበት ዘመን ነበር።

እብሪቱም ገዢውን መንግሥት ለውድቀት የዳረገበት፣ ቴክኖሎጂውና ማሕበራዊ ሚዲያው ለትውልዱ "የእስትንፋስ" ያህል የቀረበበት፣ የሥራ ተነሳሽነት መንፈስ በአያሌው እየተዳከመ በአቋራጭ መክበር እንደ ስኬት የሚታይበት፣ የብሔረተኝነት መንፈስ "ከአበባ ወደ ምርት" ፈጥኖ የተሸጋገረበትና ሽበርተኝነት፣ መፈናቀልና ግድያ የተለመደ የዕለት ተዕለት ክስተትና ዜና የሆነበት ዘመን ነበር።

የኖቤል ሽልማት ለአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተበረከተበት፣ ሳተላይቶች የመጠቁበት፣ የሰሜኑ ጦርነት ትውልዱን እምሽክ አድርጎ የበላበት። ኢትዮጵያ በዓለም የዲፕሎማሲ መድረክ ፊት የተነሳችበት፣ ግዙፍ አገራዊ የልማት ሥራዎች የተስተዋሉበት፣ የሥርዓተ መንግሥቱ ርዕይና አካሄድ ጥርትና ኩልል ብሎ ስለመፍሰሱ ግራ ያጋባበት፣ ዓለም አቀፉ የኮረና ወረርሽኝ ደጃፍ ያዘጋበት፣ የኑሮ ጫና እንደ ወስከንባይ በሕዝቡ ላይ የተጫነበት፣ እና የሕዝብ ጥያቄ የበረከተበት ሲሆን የአራተኛው ትውልድ ቅጥያና በክፍል ሁለት ገቢርነት ሊታይ የሚችል ነው። ብዙም ማለት ገና ያልጠለሉ ብዙ ጉዳዮች ስላሉ ይህንን የትውልድ ዘመን በይደር ማቆየቱ ይበጃል።

በሰማንያ ዓመት ውስጥ ልክ እንደኛ ከፊውዳሊዝም ወደ "ሶሻሊስት ነኝ ባይ" አምባገነናዊ ወታደራዊ አገዛዝ፣ ብሎም ወደ ብሔር ፖለቲካ፣ እናም "ዲሞክራሲን" አቀነቅናለሁ ወደሚል ሥርዓት የተሸጋገሩ ሌሎች አገራት ስለመኖራቸው ወደፊት ጥናት አድርገን እንመለስበታለን። በአምስቱም ዘመናት ውስጥ በጋራ አገር ከመገንባት ይልቅ በየግል አገር ለማፍረስ የተለያዩ ሙከራዎች የተደረጉባቸው ታሪኮቻችን መልካቸውም ብዛታቸውም የትዬለሌ ሊባል የሚችል ነው።

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው፡- "አንድ ትውልድ የሚሸፍነው ስንት ዓመት ነው? ከትውልድ ትውልድ የመሸጋገሪያ መለያ ድንበሩስ ምንድን ነው?" - ቁርጥ ያለ መልስ ያልተሰጣቸውን እነዚህን ሁለት ዋና ጥያቄዎች ለመመለስ አዳጋችም ከባድም ነው። ወደፊት ብዙ ጥናትና ምርምር እንደሚጠይቁም ጠቁመን እናልፋለን። በነጥቦቹ ላይ ደፈር ብለን ብንወያይባቸው ይጠቅመናል። ሰላም ለአገሬ፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

> **"አንድ ትውልድ የሚሸፍነው ስንት ዓመት ነው? ከትውልድ ትውልድ የመሸጋገሪያ መለያ ድንበሩስ ምንድን ነው?" - ቁርጥ ያለ መልስ ያልተሰጣቸውን እነዚህን ሁለት ዋና ጥያቄዎች ለመመለስ አዳጋችም ከባድም ነው። ወደፊት ብዙ ጥናትና ምርምር እንደሚጠይቁም ጠቁመን እናልፋለን። በነጥቦቹ ላይ ደፈር ብለን ብንወያይባቸው ይጠቅመናል**

# ወቅታዊ

# ‹‹በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ባለሃብቶች ኢኮኖሚውን በሞኖፖል የሚይዙበት ዕድል የለም››

- አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል
የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ፣ ብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ ዕዳና ሃብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እና የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ተጠሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች ናቸው።

ይህ ተቋም እነዚህን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በመምራት ኦዲት ሪፖርቶች ማፅደቅ፣ በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን መከታተል፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ማድረግ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና የኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓትን መዘርጋት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፣ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፣ አዳዲስ የኢንቨስትመንት መስኮችን እና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እንዲፈቀድ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ፣ እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፣ የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ማዘጋጀት ከሚተገብራቸው ተግባራቶቹ ውስጥ ናቸው።

በተጨማሪም በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግሥት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ተግባራዊነቱን መከታተል፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ለገንዘብ ሚኒስቴር ምክረ ሀሳብ ማቅረብ፣ አፈጻጸሙን መከታተል፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም እና ሁኔታ የሚያሳይ የመረጃ ሥርዓት ማደራጀት፣ የፋይናንስ አጠቃቀማቸው፣ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን በቅርበት በመከታተል የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር ማቅረብ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ ያደርጋል። የተገኘውን የምርምና እና የፈጠራ ውጤት እንዲያሰራጩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚመለከቱ መረጃዎች ማዕከላዊ አስቀማጭ ሆኖ ማገልገል፣ የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም የሚመለከቱ የውል መረጃዎችን ማሳወቅ ከተግባራቶቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

እነዚህን የልማት ድርጅቶችን በመምራት በርካታ ተግባራትን ያከናውል። ለአብነትም የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ማድረግ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና የኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓትን መዘርጋት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፣ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፣ አዳዲስ የኢንቨስትመንት መስኮችን እና የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በማጥናት እንዲፈቀድ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብን ያካትታል።

በተጨማሪም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ፣ እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ለመንግሥት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን ማረጋገጥ፣ ዕቅዶቹን ማፅደቅ፣ አፈጻጸማቸውን መቆጣጠር፣ መከታተል፣ መገምገም፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርቶች ማፅደቅ እና በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን መከታተል ከሚያከናውናቸው ተግባራትም ጥቂቶቹ ናቸው። የዝግጅት ክፍላችን የተቋሙን የሥራ እንቅስቃሴን በተመለከተ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል




ጋር ቆይታ አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ታሪካቸው ምን ይመስላል?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከ100 ዓመት በላይ አስቆጥረዋል። በአራት ምዕራፎችም የተቋቋሙ ወይንም ገጽታ ያላቸው ናቸው። በንጉስ አጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን፣ በደርግ ዘመን፣ በኢህዴግ እና ከለውጡ ወዲህ የተመሰረቱ ናቸው። በኃይለስላሴ ጊዜ የነበሩት በቁጥር በጣም ጥቂት ሲሆኑ፤ የነፃ ገበያን ማቆጥቆጥ ተከትሎ የመጡ ናቸው። ነፃ ኢኮኖሚ እያበበ የነበረበት ወቅት ሲሆን መንግስት ብዙ ሚና ነበረው። በደርግ ዘመን ደግሞ አቆጥቁጠው የነበሩትን የግል ባለሃብቶችን ሃብት በመውረስና ሶሻሊዝምን እንደ ፍልስፍና በመቁጠር ብዙውን ሃብት ጠቅልሎ የያዘ ሲሆን መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ትልቅ ሚና ነበረው። ብዙ ኮርፖሬሽኖችም የተፈጠሩበትም ነበር።

ሌላኛው ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ የነበረው ሲሆን የመንግስትን ድርሻ ለመቀነስና አብዛኛዎቹ በመንግስት እጅ ወደ ግል የተዘዋወሩበትና የመጀመሪያው የፕራይቬታይዜሽን ሂደት የጀመረበት ነው። ኮርፖሬሽኖችና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንደገና የተዋቀሩበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት 320 የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፕራይቬታይዝ ተደርገዋል። በዘመነ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ከመሳሰሉት በስተቀር በርካቶች ትርፋማ አልነበሩም።

አራተኛው ምዕራፍ ከአራት ዓመት በፊት በተጀመረው የሪፎርም ሥራ ሲሆን፤ በዚህ ወቅትም በርካቶች በኪሳራ ውስጥ ነበሩ። ሆኖም አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም በመተግበሩ ተቋሙም በአዲስ መንገድ የተቋቋመበት ነው። በዚህም ድርጅቶች ተወዳዳሪና ትርፋማ እንዲሆኑ የተጀመረበት ሂደት ነው። የድርጅቶቹ የማኔጅመንትና የፋይናንስ ሥርዓቱም በአግባቡ መሰራት የጀመረበት ወቅት ነው። በተለያዩ ወቅቶችም የተለያዩ አደረጃጀቶችን ያለፈ ተቋም ነው።

**ከእነዚህ ውስጥ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተሳሰፈው 87 ከመቶ ነው። 13 ከመቶ የሚሆነው የተሳሰፈው ለውጭ ባለሃብቶች ነው**

**አዲስ ዘመን፡- ከሪፎርሙ ወዲህ የአገርን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ የተከናወኑ አንኳር ሥራዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ከተተገበረ ጀምሮ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። የመጀመሪያው በሦስት ዘርፎች ላይ የትኩረት ነጥቦች ለይተን የልማት ድርጅቶችን ስንደግፍ ነበር። የመጀመሪያው ‹‹ፖርትፎሊዮ›› ማኔጅመንት ነው። ይህ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የልማት ድርጅቶችን ሥምሪትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ነው። ሌላው የድርጅቶቹን አስተዳደር ማስተካከል ሲሆን ሦስተኛው የተቋሙን አቅም ማጠናከር ነው።

‹‹ፖርትፎሊዮ›› ማኔጅመንት አኳያ ከለውጡ በፊት በርካታ የልማት ድርጅቶች ከሳሪና አክሳሪ የነበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ አገርን ችግር ውስጥ የከተቱም ነበሩ። እነዚህን ወደትርፋማናት የመመለስ ሥራ ነበር። ለዚህም አስዳደሩን ማስተካከል ይገባ ነበር። ለዚህም የኮርፖሬት አስተዳደር በሁሉም የልማት ድርጅት መተግበር ነበረብን። ቦርዶችም ሲዋቀሩ በዚህ ደረጃ የተቃኙ ነበሩ። የልማት ድርጅቶችም የበለጠ ውጤታማ የማድረግና መንግስት የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አካሄድ መከተል ችለናል። የግል ባለሃብቱ የሚሰማራበትን ኢኮኖሚ ክፍል ማድረግ ተችሏል። የኢትዮ-ቴሌኮምን በአብነት ማንሳት ይቻላል። ገበያውን ነፃ ተደርጓል። የአቅም ግንባታን በተመለከተ 16 የኢኒሼቲቭ እርምጃዎች ተቀርፀው ተተግብረዋል። ዓለም አቀፍና ተወዳዳሪ በሆኑ ተቋማት አቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፤ በአሁኑ ወቅትም እንደቀጠለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሪፎርሙ በፊት ትርፋ ያልሆኑና አሁን ወደ ትርፍ ህዳግ የመጡት እነማን ነበሩ፤ እንዴትስ ትርፋማ ሆኑ?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ወደ ሪፎርም ከመግባቱ በፊት በስሩ 36 ድርጅቶች ነበሩ፤ አሁን ያሉት ዘጠኝ ናቸው። በዘጠኙ ላይ አትኩሬ ለመናገር ያክል በከፍተኛ ችግር ውስጥ ከነበሩት አንዱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነበር። በነበረው ከፍተኛ የሆነ አመራር፤ አደረጃጀትና አሰራር ችግር የተነሳ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነበር። ባንኩ በዚህም መክሰርና የተበላሸ ብድር ያለው ባንክ ብቻ ሳይሆን ሊዘጋ የተቃረበ ነበር።

ይህ ባንክ በ1900 ዓ.ም ሲቋቋም ጀምሮ የመንግስትን ፖሊሲ ለማስፈጸም የተቋቋመ ሲሆን በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል። ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ የግለሰቦች ዓላማ ማስፈፀሚያ በመሆኑ ብዙ ቢሊዮን ሃብት ባክኗል፤ ከስሯል። በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠርና ወደኪሳራ የገቡ ፕሮጀክቶችን እንዲሸከም የተደረገበት የአመራርና የአሰራር ክፍተት የነበረበት ነው። ይህን ባንክ ለመታደግ መጀመሪያ የተደረገው የአመራር ለውጥ ማድረግ ነበር። ቀጥሎ አመራሩ፣ አሰራር እና አደረጃጀት ለውጥ በማድረጉ ከሁለት ዓመት በፊት ጀምሮ ወደ ትክክለኛ መንገድ ተመልሷል። የኪሳራ እና የተበላሸ ታሪክ ቀርቶ ትርፋማ የሆነ ባንክ ነው።

ሌላው የኢትዮ-ኢንጅነሪንግ ግሩፕ በቀድሞ ስሙ ሜቴክ ነው። ይህ ተቋም ለራሱ መጥፋት ብቻ ሳይሆን አገርን ይዞ ሊጠፋ የነበረ ተቋም ነው። ትልልቅና በቢሊዮን የሚቆጠር ፕሮጀክቶችን እንዲያስተዳድር ተደርጎ የነበረ ነው። አቅምና ብቃት ሳይኖር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ሳይዘረጋ ቢሊዮኖች የፈሰሱበትን ፕሮጀክት ለማስተዳደር ሲንቀሳቀስ ነበር። የዚህ ደግሞ በጣም የከፋ ነበር። የውስጥ ቁጥጥር፤ የማኔጅመንት፣ ሃብት አስተዳደር የሌለው ሃብትና ሥራው በግልጽ የማይታወቅ እና ሌሎች ችግሮች ነበሩበት። የአመራር፣ አሰራርና አደረጃጀት ችግሮቹ ከፍተኛ ነበር።

ኢንዱስትሪውን የሚመጥን የሰው ኃይል ሳይሆን የግለሰቦችን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ ነበር። ይህ መክሰር ብቻ ሳይሆን ግዙፍ ተቋም የሚመስል ግን የህዝብን ሃብት ይዞ እየሰጠመ የነበረ ተቋም ነው። እነዚህን ችግሮች በማስተካከል በዚህ ዓመት ወደ አትራፊነት መጥቷል።

የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት 128 ዓመት ያስቆጠረና ኢትዮጵያን በመላ ዓለም ያስተዋወቀ ተቋም የነበረ ሲሆን

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



መክሰር ያልነበረበት ግን በኪሣራ ውስጥ የቆየ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ወደትርፋማነት መጥቷል። ሌሎችም በዚህ መልኩ ውጤታማ እየሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ልማት ባንክ ኪሳራ ውስጥ የነበረ ተቋም ነው። የተበላሸ ብድርና በቢሊዮን የሚቆጠር ኪሣራ ኃላፊነትን ማን ወሰደ?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** የልማት ባንክ የተበላሸ ብድር ስንል በተለያየ መንገድ ይገለፃል። ለምሳሌ አንዳንድ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች የውጭ ባለሃብቶች ይዘዋቸው የነበሩና ትልልቅ የሆኑና የባንኩን 50 እስከ 60 ከመቶ ሃብት የሚይዙት ሲሆኑ ባንኩ ወደ ትርፋማነት የመጣው እነዚህን ማስተዳደር በመቻሉ ነው። ጥለው ከአገር የወጡና የከሰሩም አሉ። እነዚህን ተረክቦ ወደ ጤናማነት መመለስ ችሏል።

ከዚህ ውጭ ግን በአሰራር የተበላሹ ብሎ መንግስት በዋስትና የያዛቸውንና እያስከበረ ያለበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ በጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ክልል በእርሻ ሥም ብድር የተወሰዱበትን መንግስት ይዟቸው ለሌሎች ለማስተላለፍ እየሠራ ነው። መንግስት ለመጠባበቂያ ብሎ የያዘውን በመጠቀም ወደ ትርፍም እየመጡ ነው። ከዚህ ውጭ ደግሞ ወደ ህግ የሄዱም አሉ። እርሻዎቹ አሁንም በባንኩ እጅ ናቸው፤ ወደ ሌሎች ባለሃብቶች የማስተላለፍ ሂደት ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ትርፋማ የሆኑ ተቋማት የስኬታቸው ሚስጥር ምን ነበር?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** በእኛ ሥር ያሉት ውስብስብ ችግር የነበረባቸው ዕዳ እና ውዝፍ ስራ የነበረባቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ስትራቴጂካሊ የፖሊሲ ስራዎች ናቸው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ትርፋማ ይሆናሉ ብለን የማንጠብቃቸው ግን የፋይናንስ ጤናማነታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ የምናደርጋቸው ናቸው። ልማት ባንክ ትርፋማነቱን ጠብቆ ይሄዳል። የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ትርፋማ እየሆኑ ይመጣሉ።

ኢትዮ ኢንጅነሪንግ በተመሳሳይ መንገድ ትርፋማ ይሆናል። ግን የዚህ ትልቁ ችግር በስሩ ያሉ ዘጠኝ ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙት ውጭ ግብዓት ነው። አሁን የዕዳና ካፒታል ማሻሻያ እየተደረገለት ነው። ትርፋማ የሆኑት የተሻለ ልምድ እንዲቀስሙም እየተደረገ ነው። ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ኢትዮጵያ አየር መንገድ ልምድ እየወሰዱ ነው። ዓለም አቀፍ ተቋማትንም በመቅጠርም ስልጠና እየሰጠን ነው። ከጀርመን ፍራንክፈርት ማኔጅመንት ትምህርት ቤት ጋር በመነጋገር ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ ኢንተርፕራይዞች ላሏቸው ክልል ለአንድ ዓመት የሚዘልቅ በ21 ርዕሶች ላይ ስልጠና እየሰጠን ነው። እስካሁን 10 ስልጠና ሰጥተናል። ይህ የልማት ድርጅቶችን ትርፋማ የሚያደርግና ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ ያስችላቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግስት የልማት ድርጅቶች አንዱ ችግር የነበረው የውስጥ ኦዲት ደካማ መሆኑን የህዝብ እንደራሴዎች በተደጋጋሚ ሲያነሱት ነበር። ይህ አሁን ተሻሽሏል?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** አንድ ተቋም ትክክለኛ የፋይናንስ ተቋም ነው የሚባለው የፋይናንስ ሁኔታው ሲታወቅ ነው። ስለዚህ የእኛ ትልቁ ስራ የነበረው የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ነው። የልማት ድርጅቶች ወቅታዊ ሂሳብ እንዲኖራቸው ነው በዚህም በጣም ሰርተናል። የኦዲት ባክሎክ እንዲዘጋ ተደርጓል። ኢትዮ ኢንጅነሪንግን ጨምሮ ይህ ተሰርቷል። ኢትዮ ኢንጅነሪንግ እስከ 2012 ዓ.ም ሂሳቡን እየዘጋ እያፀዳ ነው። የኋላ የሂሳብ ታሪኩን እየዘጋ 2013 እና 2014 ዓ.ም ይቀራቸዋል። ግን ቀድሞ የነበረውን እየዘጉ አሁን እየተሻሻሉ ነው። ሂሳብ መያዝና ሰነድ መመዝገብ ከማይቻልበት ታሪክ ወጥተዋል። ከኋላ ታሪኩ የተነሳ የኦዲት ሁኔታው ችግር ያለበት ቢሆንም ችግሮችን ለማስተካከል እየሄደ ነው።

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ከሰርቨሩ ላይ የነበረው ዳታ ሙሉ ለሙሉ እንዲጠፋ ተደርጓል። ይህ ሆን ተብሎ መረጃው እንዲጠፋ የተደረገበት ነው። በዚህም ከ3 እስከ 4 ሚሊዮን የሚጠጋ ሰነድ በእጅ አንድ በአንድ ሰብስቦ በመመዝገብ ሂሳባቸውን ወቅታዊ ለማድረግ እየሰሩ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ሂሳባቸውን በወቅቱ መዝጋት ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ አሰራር እያዘመኑት ነው። ብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ከግድፈትም ነፃ የሆነ ኦዲት ናቸው። የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ዕዳና ሃብት አስተዳደር ኮርፖሬሽንና ሌሎች ድርጅቶችም ዘመናዊ አሰራር ውስጥ እየገቡ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ፕራይቬታይዝ የሚደረጉት ምን ዓይነት ድርጅቶች ናቸው?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** ቀደም ብሎ ሲሠራ በነበረው ሁኔታ 320 ድርጅቶች ፕራይቬታይዝ ተደርገዋል። አሁን ባለው አሰራር የመጀመሪያው የመንግስትን የትኩረት መስክ ዒላማ አድርገው ነው። መንግስት ገበያ ውስጥ ድርሻ ቢኖረው ጠቃሚ ይሆናል ወይ የሚለው ይታያል። አሁንም የፖሊሲ ተቋማት የምንላቸው አሉ። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ እና የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በዚህ ውስጥ የሚታዩ ናቸው።

በእርግጥ የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ፕራይቬታይዝ መሆን ይችላል፤ ግን ካለው ማበረታቻ አንፃር ደፍሮ የማይገባበት ነው። ከዚህ ውጭ መንግስት በክፍለ ኢኮኖሚው ውስጥ መቆየት አስላጊ ካልሆነ እንዲለቀቅ ይደረጋል። ዋናው የገበያ ፍላጎት ሳይሆን የሴክተሩ ጉዳይ ይታያል። ማትረፍና መክሰር ብቻ የሚታይ አይደለም። ለምሳሌ ኢትዮ ቴሌኮም በጣም አትራፊ ነው። ግን መንግስት ለነፃ ገበያ ያለው አመለካከትና ፍላጎት ያለውን ምልከታ ያሳያል። በተጨማሪም ለመንግስት የገንዘብ አቅምንም ያሳድጋል። ስለዚህ መንግስት ፕራይቬታይዝ የሚያደርገው ብዙውን ጊዜ መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ሚና እንዲቀንስና ነፃ ገበያ እንዲኖር ከመሻት ነው። ከዚህ ቀደም እርሻዎች፤ ኢንዱስትሪዎች እና ሆቴሎች ለግል ባለሃብቶች ተላልፈዋል።

አሁን ፕራይቬታይዝ ልናደርጋቸው የምናስባቸውና በመንግስት የአክሲዮን ድርሻ ተይዘው ያሉ ተቋማት አሉ። እነርሱን ባለሃብቶች እንዲገቡበት ይፈለጋል። ለምሳሌ በመንግስት እና በግል አጋርነት ያሉ እንደ ቢ.ኤም ጨርቃጨርቅ፣ አፍሪካ ጁስ፣ አብያታ ሶዳ አሽ እና አምቼ ናቸው። ሌሎች ደግሞ የመንግስትን ፍላጎት አድርገን እንሄዳለን። በእኛ ተጀምረው የነበሩ የስኳር ፋብሪካዎችም ኢትዮ-ቴሌኮም ወደ ሌላ ተቋም ሄደዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ድርጅቶች ፕራይቬታይዝ ሲደረጉ የክልል መንግስታት እና የፌደራል መንግስት አልፎ አልፎ ይገባኛል የሚሉ ጥያቄችም ይነሱበታል ይባላል። ሚናቸው የተለየ ነው?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** የመንግስት የልማት ድርጅቶች የህዝብ ናቸው። የእኛም መሪ ሐሳብ ‹‹የህዝብን ሐብት ለህዝብ›› የሚል ነው። እነዚህ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ከክልል ጋር የሚያገናኛቸው የለም። የሚቋቋሙት በአዋጅ 2584 ነው። የህዝብና የመንግስት ስለሆኑ መንግስትን ወክለን የምናስተዳድረው እኛ ነን። ግን እነዚህ ድርጅቶች በአካል በሆነ ቦታ ወይንም ክልል ይገኛሉ። ስለዚህ እንደማንኛው ዜጋ መጠቀም ይችላሉ። ግን እነዚህን ድርጅቶች የማስተዳደር ፍላጎት ቢኖሯቸው እንኳን አሰራሮች አሉ። ለምሳሌ ክልላዊ የልማት ድርጅቶች አሉ። ግን የበለጠ ትርፋማ እና ተወዳዳሪ የሚሆኑ ከሆነ መንግስት ለክልል ሊያስተላልፍ ይችላል።

ለአብነትም ባህርዳር እና ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅን ለአማራ ክልል በሽያጭ አስተላልፈናል። አርሲ እና ባሌ እርሻ ለኦሮሚያ ክልል ተላልፏል። አሰላ ብቅል ፋብሪካ ለዩኒዮኖች ተላልፏል። በየክልሎቹ የተላለፉ አሉ። ስለዚህ የልማት ድርጅቶችን አንዱ ክልል ላስተዳድር የሚልበት ነገር የለም። ግን ለአሰራር አመቺ ከሆነ መንግስት የሚጠቅመውን ያደርጋል። ስለዚህ እስካሁን እኔ ላስተዳድር ብሎ ገፍቶ የመጣ ክልል የለም። ሆኖም አልፎ አልፎ የወሰን መግፋት ይኖራል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት በመላ አገሪቱ 80 ቅርንጫፎች አሉት። በየቦታው በጣም ትልልቅ ቦታ አለው። ይህን ለሌሎች የማስተላለፍና የመግፋት ሁኔታ አለ። ይህን በመነጋገር የማስተካከል ሁኔታዎች አሉ። በአጠቃላይ ግን የወሰን፣ ይዞታ ማስከበር ላይ ግን ችግር አልፎ አልፎ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ድርጅቶች ፕራይቬታይዝ ሲደረጉ ከአገር ውስጥ ባለሃብቶች ይልቅ ወደ ውጭ ባለሃብቶች የማድላት ዝንባሌዎች አሉ የሚል ወቀሳም አለ። እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** ይህንን በመረጃ ማስደገፍ አስፈላጊ ነው። እስካሁን ከ300 በላይ ድርጅቶች ተላልፈዋል። ከግብርና 27 ድርጅቶች፣ ከኢንዱስትሪ 161፣ ቅርንጫፎችን ጨምሮ ከአገልግሎት 180 ድርጅቶች ተላልፈዋል። ከእነዚህ ለባለሃብቶች ወደ 200፣ ለሰራተኞች 45 ድርጅቶች ተላልፈዋል። ሌሎች ደግሞ በመንግስትና ባለሃብቶች የጋራ ልማት ናቸው። እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ባለው መረጃ መሰረት ከእነዚህ ውስጥ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች የተላለፈው 87 ከመቶ ነው። 13 ከመቶ የሚሆነው የተላለፈው ለውጭ ባለሃብቶች ነው። በእርግጥ ከእነዚህ ውስጥ ትንባሆ ሞኖፖልን ወስደን ብናይ በጣም ብዙ ብር ነው የያዘው። በዋጋ ብናየው ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች 315 ድርጅቶችን በአስር ቢሊዮን ብር ለአገር ውስጥ ድርጅቶች ተላልፈዋል። ለውጭ የተላለፈው 39 ቢሊዮን ብር ደግሞ የተላለፈው 13 ከመቶ የሚሆነው ነው። ስለዚህ መንግስት ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ትልቅ ድጋፍ ያደርጋል።

የውጭ ባለሃብቶች ሲመጡ ግን የውጭ ምንዛሪ፣ የዕውቀት ሽግግር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ከግምት ውስጥ ይገባል። ከዚህ ውጭ ግን ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሃብቶች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር በተከታታይ ለአምስት ዓመታት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል። በቢዝነስ ፕላናቸው መሠረት መሄዳቸውን ይከታተላል፤ በዚህም አብዛኞቹ ውጤታማ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የታዳጊ አገራት ድርጅቶች ‹‹ፕራይቬታይዝ›› ሲደረጉ በምዕራባውያን በመጠቀለል በአገራት ሉዓላዊነትና ነጻነት ይጋፋል የሚል የምሁራን ትችት አለ። በዚህ ረገድ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** ኢትዮጵያ በዚህ አትታማም። ከለውጡ ወዲህም የተሄደበት መንድ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የኢኮኖሚ ስብራትን ማስተካከል ነው። ለዚህ ደግሞ እነዚህ ሴክተሮች ወሳኝ ናቸው። ባደጉትም አገራት ጭምር ይህ ሴክተር ትልቅ ግምትና ዋጋ አለው። መንግስት ይህን በጥንቃቄ ነው የሚሰራው። ከውጭ ያለው ጫና እያንዳንዱ ሴክተር ክፍት ይደረግ የሚል ነው። ነገር ግን አገራችን ሁሌም ጥንካሬዋን የምታሳይበትና የጽናቷ ሚስጥር የለውጥ እሳቤዎች ይህን አጠንክረው የሚሄዱ ናቸው። የህዝብና አገር ጥቅም የሚያስከብር ስራ ብቻ ነው የሚሰራው። ይህ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጠንካራ አቋም ነው።

አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ባለሃብቶች ኢኮኖሚውን በሞኖፖል የሚይዙበት ዕድል የለም። የሚቀረጹ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና አፈጻጸም ሂደቶችም ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው። ውድድርን በማያቀጭጭ መልኩ ነው የምንሰራው። የአፍሪካ አገራት ያለፉበትን መንግስት እናውቃለን። እኛ ይህን በማወቃችን ጥንቃቄ የተወሰደበት ነው፤ በቀጣይም ክፍት ለሚደረጉት መንግስት በልዩ ትኩረትና ጥናት ነው የሚያካሂደው። ለኢኮኖሚ ወሳኝ የሆኑ ተቋማት አሁንም ክፍት አልተደረጉም። የፕራይቬታዜሽን ህጋችንም ጠንካራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምዕራባውያን በመንግሥት ላይ ጫና እያደረጉ አይደለምን?**

**አቶ ሐብታሙ፡-** የምናየው ነገር ነው። የፋይናንስ ተቋማትን ክፍት አድርጉ የሚል ከፍተኛ ግፊት አለ። መንግስት ጥናት እያደረገ ነው። ጥናት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ነው። ዘግተን የማናቆያቸው ሴክተሮች አሉ። ነገር ግን በመንግስት በቂ ዝግጅት እና ጥናት ከተደረገ በኋላ የሚወሰን ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እያመሰገንኩ ተጨማሪ ሐሳብ ካለ ዕድሉን ይጠቀሙ።**

**አቶ ሐብታሙ፡-** አመሰግናለሁ። የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ስምሪት ውጤታማ ለማድረግ አቅደን እየሰራን ነው። የሁሉም ድርጅቶች ሪፎርም በታሰበው ልክ እንዲሄድ የተጀመረው ጥረት በጣም ጥሩ የሚባል ነው። የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሂሳብ አያያዛቸውና ግልፀኝነት እንዲኖረውና ጠንካራ እንዲሆን እየሰራን ነው። ማኔጅመንቱንም አጠናክረን እንቀጥላለን። በየጊዜው እየዘመነ ይሄዳል። የሃብት ጥራታቸውም በፈጠራ የታገዙ እንዲሆኑ ይደረጋል። በአሁኑ ወቅት ዘጠኙ ድርጅቶች ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ ሃብት እያንቀሳቀሱ ነው።

በቀጣይ ለአገሪቱ ምጣኔ ሃብት ላይ ትልቅ አበርክቶ እንዲኖራቸው በትኩረት የሚሠራ ይሆናል። በኪሳራ ውስጥ የነበሩ ድርጅቶችም ወደ ትርፋማነት እየመጡ ነው። ይህም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና እየቀነሰ ይሄድ ይሆናል እንጂ ወሳኝ በሚባሉት ላይ እጁን ማስገባቱ አይቀርም። ቻይና እና ፈረንሳይም በዚህ ደረጃ ነው ያሉት። የአገር ኢኮኖሚ ችግር ሲገጥመው፤ ለመፍትሄው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚና በጣም ትልቅ ነው። በመሆኑም የእኛ የልማት ድርጅቶችም ኢኮኖሚውን በመደገፍ ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ነው። ስለዚህ በቀጣይም ይህ ሥራ በተጠናከረ መንገድ የሚከናወን ይሆናል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት - ለኢንቨስትመንት እድገት

አንተነህ ቸሬ

ከቅኝ ግዛት ነፃ ያልወጡ አፍሪካውያንን ከቅኝ ተገዢነት ለማላቀቅና የአፍሪካን የምጣኔ ሀብትና የፖለቲካ ውህደት ለማሳካት የተመሰረተውን የቀድሞውን ‹‹የአፍሪካ አንድነት ድርጅት››ን (Organization of African Unity - OAU) እ.ኤ.አ በ2002 ከተካው የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት (African Union - AU) ዓላማዎች መካከል አንዱ በምጣኔ ሀብት ያደገችና የበለጸገች አፍሪካን እውን ማድረግ ነው። በእርግጥ የምጣኔ ሀብት ዘርፍን ጨምሮ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዘመን የነበረችው አፍሪካ፣ በአፍሪካ ኅብረት ዘመን ካለችው በብዙ መልኩ የተለየችና የተሻለች መሆኗ አይካድም። ባለፉት ዓመታት በኢኮኖሚዋ እያደገች፣ ትናንት ከነበራት የምጣኔ ሀብት ትስስር የተሻለ ለውጥ እያስመዘገበች ትገኛለች።

ይሁን እንጂ ካላት እምቅ አቅም ብዙ ችግሮች አንፃር አህጉሪቱ የምትገኝበት የምጣኔ ሀብት ደረጃ ዝቅተኛ ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የአህጉሪቱ አገራት ለዜጎቻቸው መሰረታዊ የሚባሉ ሸቀጦችን ጭምር የሚያቀርቡት ከውጭ ገዝተው እንጂ ራሳቸው አምርተው አይደለም። የአፍሪካ ሀገራት የእርስ በእርስ የንግድ ልውውጣቸው 14 በመቶ ብቻ ነው። ይህ አሃዝ የሌሎች አህጉራት ሀገሮች ከሚያደርጉት አህጉራዊ የእርስ በእርስ የንግድ ልውውጥ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። ለአብነት ያህል የአውሮፓ ሀገራት አህጉራዊ የእርስ በእርስ የንግድ ልውውጣቸው 62 በመቶ ሲሆን፣ የሰሜን አሜሪካ ሀገራት 40 በመቶ እና የእስያ ሀገራት 30 በመቶ ነው።

የአፍሪካን የንግድና የምጣኔ ሀብት ትስስር እውን ለማድረግ ያግዛሉ ከተባሉ ግብዓቶች መካከል አንዱ ‹‹የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት›› (African Continental Free Trade Area Agreement - AfCFTA) መሆኑ ይገለጻል። ስምምነቱ በአፍሪካ ሀገራት መካከል የሚደረጉ የንግድ ልውውጦችን ለማቀላጠፍና የግብይት መሰናክሎችን ለማስቀረት እንደሚያስችል ተስፋ ተጥሎበታል፤ አብዛኞቹን የንግድ ታሪፎች በማስቀረት የአፍሪካውያንን የእርስ በእርስ ንግድ እስከ 2034 (እ.ኤ.አ) 60 በመቶ በማሳደግ የሦስት ነጥብ አራት ትሪሊዮን ዶላር ገበያ የመፍጠር እቅድ አለው። ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ገቢራዊ ከሆነ፣ በዓለም ባንክ ስሌት መሠረት 30 ሚሊዮን አፍሪካውያንን ከከፋ ድህነት፤ 70 ሚሊዮን የአህጉሪቱን ዜጎች ደግሞ ከመካከለኛ ድህነት ያወጣል።

ስምምነቱ በአህጉሪቱ የሚታየውን የተዛባና ያልተመጣጠነ የንግድ ስርዓት በማረም ሂደት ላይ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ለሚሊዮን ዜጎችም ተጨማሪ የስራ እድል ይፈጥራል። ለአፍሪካ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ውህደትም በር ይከፍታል ተብሎ ይታሰባል። የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ከሚፈጥረው የኢኮኖሚ እድገት ባሻገር፣ በተለያዩ የአህጉሪቱ ክፍሎች የሚስተዋሉ ግጭቶችን ለመቀነስ ለሚደረገው ጥረት አጋዥ ይሆናል ተብሎም ይጠበቃል።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት መልካም እድል ይፈጥርላቸዋል ተብሎ ከሚጠበቁት ዘርፎች መካከል አንዱ የኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አረጋ ሹመቴ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት የሥራ እድሎችን በመፍጠር፣ ኢንቨስትመንትን በማሳደግ እና የንግድ ትስስርን በማጠናከር ለአፍሪካ የምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይገልፃሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ በኢንቨስትመንት ስራዎች አማካኝነት ለሚመረቱና ለገበያ ለሚቀርቡ ምርቶች በቂ ገበያ እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህም የገበያ እጥረትን ይቀርፋል። አንዳንድ ሀገራት ከፍተኛ የሆነ የጥሬ እቃ አቅርቦት ስላላቸው በነፃ የንግድ ቀጠናው ምክንያት በሚፈጠረው የንግድ ትስስር በኩል ጥሬ እቃዎችን በቀላሉና በተሻለ መልኩ ማግኘት ይቻላሉ።

የንግድ እንቅስቃሴው በነፃነት ሲከናወን የምርት ግብዓቶችና ምርቶች ያለተጨማሪ ወጪ ለኢንቨስተሮች ይቀርባሉ። ይህም የማምረቻ ወጪ እንዲቀንስ ያደርጋል። የማምረቻ ወጪ መቀነስ የመሸጫ ዋጋ እንዲቀንስ በማድረግ ለዋጋ መረጋጋት የራሱን በጎ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

ከሌሎች ሀገራት ባለሀብቶችና ተቋማት (ምናልባትም ከምዕራባውያን) ጋር በሽርክና የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ስራዎች ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት እንዲመጡ እድል ሊፈጥር እንደሚችልም ነው የጠቀሱት። ስምምነቱ የሚፈጥረው ሰፊ የገበያ እድል የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ አቅም ያላቸው የአውሮፓ፣ የአሜሪካና የእስያ ባለሀብቶች ወደ አፍሪካ እንዲመጡ ሊያደርጋቸው ይችላል ብለዋል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ በበኩላቸው የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ዘርፉ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ይገልፃሉ። ስምምነቱ የገበያ አማራጮችን ከማስፋት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ከማድረግ፣ ኢንቨስትመንትን ከማሳደግ እና መልካም ተሞክሮዎችን ከመለዋወጥ አንፃር በርካታ አዎንታዊ አስተዋጽኦዎችን ያበረክታል ይላሉ።

ዶክተር ሞላ ስምምነቱ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ስለሚኖረው አዎንታዊ ሚና ሲያብራሩ ‹‹የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑበት ቀጠና ሲሰፋ የተለየ የቴክኖሎጂ፣ የኢንቨስትመንት፣ የአስተሳሰብ (እውቀት) እና የፍላጎት ተሞክሮ ይገኛል። የተሻለ የምጣኔ ሀብት ከንውን ቅልጥፍና ይኖራል። ይህ ደግሞ የኢንቨስትመንት ፍሰት የተሻለ እንዲሆን ያደርጋል።›› ሲሉ ያብራራሉ። አንድ የኢንቨስትመንት ስራ በአንድ ሀገር ላይ ብቻ ሲከናወን እና በብዙ ሀገራት ሲስፋፋ የሚኖረው የውጤት ልዩነት ይታወቃል ያሉት ዶክተር ሞላ፣ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ ሰፊ በሆነ ወሰን ስለሚከናወን በስምምነቱ በኩል የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ስራዎች ትልቅ ውጤት ያስገኛሉ ነው የሚሉት።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ስምምነቱ ቀጣይነት ያላቸው፣ ባለግዙፍ ካፒታል የሆኑና የተሻለ የሥራ እድል መፍጠር የሚችሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለመጋበዝ እድል ይፈጥራል። በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱ ሕግጋት ለኢንቨስተሮች የተሻለ ዋስትና ስለሚሰጡ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚኖራቸው ፍላጎት ይጨምራል፤ ይህም የሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲያድግ ያስችላል።

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራ ብዙ ቅድመ ሁኔታዎችንና ዝግጅቶችን ይፈልጋል። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ከአፍሪካውያን ዜጎች፣ ባለሀብቶችና መንግሥታት የሚጠበቁ ዝግጅቶች ሲሆኑ የስምምነቱን ውጤታማነት የሚወስኑም ይሆናል። በተለይ የኢትዮጵያ መንግሥትና ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እንዲሁም ዜጎች ከስምምነቱ ተጠቃሚ ለመሆን ዘርፈ ብዙ ዝግጅቶችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ ረገድ መንግሥት፣ ባለሀብቶችና ዜጎች (ሰራተኞች) የየራሳቸውን ዝግጅት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ዶክተር አረጋ ያስገነዝባሉ። መንግሥት መዋቅራዊ አሰራሮችን እና መመሪያዎችን ለኢንቨስተሮቹም ሆነ ለመንግሥት አካላት ግልፅነት በተሞላበት መልኩ የማሳለጥ፣ የማስተካከልና የማጠናከር፤ ባለሀብቶች በቀላሉና ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ እንዲያመርቱና ምርቶቻቸውን ወደ አፍሪካ ገበያ እንዲያቀርቡ ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና መሰረተ ልማቶችን (የሰው ኃይል፣ የኃይል አቅርቦት፣ ውሃ፣ መንገድ…) የማሟላትና ዝግጁ የማድረግ እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና መምራት የሚችሉ ብቁ የሆኑ ሰራተኞችን የማዘጋጀት ኃላፊነቶች አሉበት። ስለዓለም አቀፍ ንግድ እና ስለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ለሚመለከተው የሥራ ፈጣሪ ማኅበረሰብ ማጋራት ይኖርበታል ሲሉ ያመለክታሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መረጋጋትን መፍጠር ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ አለመረጋጋቶች አሉ። እነዚህ አለመረጋጋቶች ባሉበት ሁኔታ ኢንቨስትመንት ላይ የመሳተፍ ፍላጎት ያለው ባለሀብት ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ለአለመረጋጋቶቹ መፍትሄ በማበጀት ሰላማዊ ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ሕግና የአሰራር መመሪያዎችም በትክክል መዘጋጀት አለባቸው። ምክንያቱም አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ ሲተገበር አዳዲስ አሰራሮችንና የግብይት ስርዓቶችን መከተል ስለሚያስፈልግና አሰራሩም ሀገሪቱ ለረጅም ጊዜያት ስትጠቀምበት የነበረውን የንግድ ስርዓት በተወሰነ መልኩ የሚቀይር ስለሆነ የስምምነቱን አሰራሮች ባማከለ መልኩ አዳዲስ የሕግና የአሰራር መመሪያዎችን መዘጋጀት ያስፈልጋል›› ይላሉ።

**ስምምነቱ ቀጣይነት ያላቸው፣ ባለግዙፍ ካፒታል የሆኑና የተሻለ የሥራ እድል መፍጠር የሚችሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለመጋበዝ እድል ይፈጥራል፡፡ በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱ ሕግጋት ለኢንቨስተሮች የተሻለ ዋስትና ስለሚሰጡ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚኖራቸው ፍላጎት ይጨምራል፤ ይህም የሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲያድግ ያስችላል**

ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች በገንዘብ፣ በአመራር እውቀት፣ በስራ ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ትግበራ ራሳቸውን ለተወዳዳሪነት ማዘጋጀት አለባቸው። ከአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት የሚመጡ ባለሀብቶች የተሻለ ዓለም አቀፍ ተሞክሮና ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ተወዳዳሪነት እንዲኖራቸውና አሸንፈው መውጣት እንዲችሉ የገንዘብ፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ አቅማቸውን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል። ከመንግሥት አካላት ጋር ተደጋጋሚ ውይይት ሊያደርጉና አብሮ የመስራት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። መንግሥትም ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ አለበት።

“የመንግሥት ዋና ሚና ስምምነቱ እንዲተገበር ማመቻቸትና ማሳለጥ ነው” የሚሉት ዶክተር ሞላ፣ የንግድ ሕግጋትን ከስምምነቱ መመሪያዎች ጋር በማጣጣም የኢንቨስትመንት ምኅዳሩን ምቹ የማድረግ እንዲሁም ስለስምምነቱ በቂ ግንዛቤ የመፍጠር ኃላፊነት እንዳለበት ያስረዳሉ። ቀጠናዊ ትስስሩ በሰፋ ቁጥሩ ውድድሩ ቀላል እንደማይሆንም ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የገንዘብ፣ የእውቀትና የአመራር አቅማቸውን በማሳደግ ራሳቸውን ለውድድር ዝግጁ ማድረግ እንዳለባቸውም ይመክራሉ።

አፍሪካ በርካታ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ያሉባት አህጉር በመሆኗ የነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ ትግበራ መሰናክሎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል የሀገራቱ የጎንዮሽ ችግሮች ተጠቃሽ እንደሆኑ ዶክተር አረጋ ያስረዳሉ። ብዙዎቹ የአፍሪካ ክፍለ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቶች ውጤታማ ከማይሆኑባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ የሀገራት የጎንዮሽ ችግሮች መብዛት ነው። አንዳንዶቹ ሀገራት የውስጥ ሰላም ስለሌላቸው የውስጥ ችግራቸውን ወደ ውጭ በማውጣትና ለችግሩን ሌሎች ወገኖችን ተጠያቂ በማድረግ ከሌሎች ሀገራት ጋር ውዝግቦችን ይፈጥራሉ። ስለሆነም መንግሥታት ለምጣኔ ሀብትና ማኅበራዊ ጉዳዮች የላቀ ትኩረት መስጠት እና የጎንዮሽና የፖለቲካ ችግሮቻቸውን በመፍታት በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ ተመስርተው መስራት አለባቸው ሲሉ ያሳስባሉ።

‹‹አንዳንዶቹ ክፍለ አህጉራዊ የንግድ ስምምነቶች ለአህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ተግዳሮቶች ሊሆኑ ይችላሉ›› የሚሉት ዶክተር አረጋ፣ አንዳንድ ሀገራት በእነዚህ ክፍለ አህጉራዊ የንግድ ስምምነቶች ላይ የበላይነት በመያዛቸውና ተጠቃሚነቱን ከፍ ባለ ድርሻ በመውሰዳቸው አህጉራዊውን ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት እንደ አደጋ ሊመለከቱት እንደሚችሉ ያስገነዝባሉ።

እንደ ዶክተር አረጋ ገለጻ፤ የአህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት መስተጋብር ብዙ ተዋንያንን ያሳትፋል። አህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት በክፍለ አህጉራዊ የንግድ ስምምነቶች ላይ የበላይነት ለያዙትና ሌላ ተወዳዳሪና የጥቅም ተጋሪ ለማይፈልጉት ለአንዳንዶቹ ሀገራት ሌሎች ተወዳዳሪዎችን ስለሚያመጣባቸው ስምምነቱ ተጠቃሚነታቸውን የሚቀንስባቸው አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። በዚህ ረገድ ክፍለ አህጉራዊ የንግድ ስምምነቶች ለአህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራና ውጤታማነት ተግዳሮት ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል ክፍለ አህጉራዊ የንግድ ስምምነቶች ለአህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት አዎንታዊ ሚና ሊኖራቸውም ይችላል። ብዙ ሀገራት በነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቶች ትግበራ ላይ የተሳተፉ ልምድ ስላላቸው ለውይይትና ለድርድር ቀለል ያለ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ዶክተር አረጋ ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ በአህጉራዊው ነፃ የንግድ ቀጠና ትግበራ ሂደት ሊያጋጥሟት ከሚችሉ ተጠባቂ ችግሮች መካከል የሰለጠነና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል፣ በቂ ቴክኖሎጂና በቂ ተወዳዳሪነት ያለው ዓለም አቀፍ ልምድ እና በዓለም አቀፍ ንግድ ተወዳዳሪነትን የለመደ የንግድ ማኅበረሰብ አለመኖር፤ የግብዓት አቅርቦት አለመስተካከል፤ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች የፈጠሯቸው መስተጓጎሎች እንዲሁም ያልተስተካከለና ዝቅተኛ የሆነ (እጥረቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የሄደ) የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት መኖር ይጠቀሳሉ።

ዶክተር ሞላ በበኩላቸው፣ ‹‹በነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቱ ‹‹እኛ ተወዳዳሪ ላንሆን እንችላለን›› የሚሉ አካላት በስምምነቱ ጥርጣሬ ሊያድርባቸው ይችላል። ስለሆነም ስለ ስምምነቱ በቂ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። ከዚህ ቀደም የወጡ ሕግጋትን ለስምምነቱ ተፈፃሚነት አመቺ በሆነ መልኩ ማሻሻልና መቀየር ይገባል። ክፍለ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነቶች ለአህጉራዊውን ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ትግበራና ስኬት መሰናክል እንዳይሆኑ የሚደርጉ አሰራሮችን መተግበር ያስፈልጋል›› በማለት ይመክራሉ።

የአፍሪካ ኅብረት ዓላማዬ ነው ብሎ የያዘውን የአህጉሪቱን ምጣኔ ሀብት የማሳደግና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር የመፍጠር ግቡን ለማሳካት፣ የአህጉሪቱን እምቅ አቅም ለመጠቀም ለሚያስችለው የእርስ በእርስ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባዋል። አህጉራዊው የምጣኔ ሀብት ትስስር አፍሪካውያን ሀብታቸውን ተጠቅመው በጋራ ለማደግ የሚያስችል እድል ይሰጣቸዋል፤ በዓለም ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ እንዲኖራቸውም ያስችላቸዋል። ይህን አህጉራዊ የእርስ በእርስ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር እውን ከሚያደርጉ ግብዓቶች መካከል አንዱ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነት ነው። ኢትዮጵያም ስምምነቱ የሚጠይቃቸውን ዘርፈ ብዙ ቅድመ ዝግጅቶች በማድረግ ከዚህ ስምምነት ትግበራ ተጠቃሚ መሆን ይጠበቅባታል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ፖለቲካ የግድ ከሆነ፤ የቱ ነው ትክክል?

ግርማ መንግሥቴ

**"ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው" ይላል የፍልስፍና አባት አርስቶትል፤ ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ (Political Animal) ከሆነና ፖለቲካም የግድ ከሆነ፣ የትኛው መስመር ይበጀዋል፤ የቱስ ነው ትክክል፣ ማንስ ነው ታማኙ፣ የቱስ ነው አስተዋይ፣ ማንስ ነው ተስተዋይ? እነዚህን ሀሳቦች ይዘን አብረን እንዘልቃለን።**

ዓለማችን አንድ መንደር ሆናለች፣ የሚያስፈልገን መከፋፈል ሳይሆን "መደመር" ነው፤ ይህ እውን የሚሆነው ደግሞ በሉዓላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ነው (ወይም አዲሱ የዓለም ሥርአት) ከምትለው አሜሪካ ጀምሮ፤ ያለው እድል አብሮ ማደግና በጋራ ተጠቃሚ መሆን ነው እስከምትለው ዘመናዊቷ ቻይና ድረስ የርእዮተ-ዓለም ጋጋታው ነጋ ጠባ ደም እንዳፋሰሰ እንጂ ሰላምን መሬት ሲያወርድ አልታየም። በተለይ የብሔር ፌደራሊዚም ነው የሚያስፈልጋችሁ በማለት የተመከሩ አገራት ፍዳቸውን እያዩ መሆኑ ጉዳዩን ዳግም ለመመርመር ያስገድዳልና መመርመር ያለበት ቢመረምረው አይከፋም።

ዓለምን ጉድ እየሰሯት ያሉት የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን ናቸው፤ በፍፁም፣ ዓለማችንን ለዚህ አይነቱ ምስቅልቅሎሽ የዳረጓት የተፈጥሮ ሳይንስ ምሁራን ናቸው የሚለው እሰጥ አገባ (እዚህ ላይ፣ ለ"ባላንስ" ሲባል፣ እናንተ በአግባቡ ብትመሯት ኖሮ እኛም የጦር መሳሪያ ተኮር ምርምሮችን ባላካሄድን ነበር የሚሉትን የተፈጥሮ ሳይንስ ምሁራንን አስተያየት ማንሳት ተገቢ ይሆናል) በተለያዩ ጊዜያት በከፍተኛ ደረጃ የመወያያ ርእሰ-ጉዳይ ሆኖ ኖሯል። ወደዛ አንገባም።

የስነልቦና አባት የሚባለው ሲግመን ፍሩድ የሁሉም ነገር መነሻ ‹‹ወሲብ›› ነው በማለት የስነምግባር ጥሰት ይፈፀም ዘንድ መሰረቱን የጣለው ሳይረሳ፤ ለዓለማችን መፍትሄው ኮሚኒዝም ብቻ ነው በማለት የኢምፔሪያሊዝምን ማጣፊያ ሥርአት የዘረጋውና ምድርን በሁለት ጎራ በመከፈል እያጠዛጠዘ የሚገኘው ካርል ሔንሪክ ማርክስ ሳይዘነጋ፤ ሰው ከዝንጀሮ ነው የመጣው በማለት ተከብሮ የኖረውን፣ የዓለምን የእምነት መሰረት በማናጋት ለሁለት የከፈለው ኢቮሊዩሽኒስቱ ዳርዊን ሳይታለፍ፤ የአውዳሚነት ባለሚሉ ፍሬደሪክ ኒች ሳይዘለል፤ (ከ"መሪ"ዎች) ተከታዮቹ እየበዙ የመጡትና ሕገመንግስት ለምኔው ኢድ አሚን ጋጋ ሳይሰረዝ . . . ሌሎችም በርካቶች ሁሉ ተደማምረው የዛሬዋ ዓለማችንን ውስብስብ አድርገዋት ይገኛሉ።

እነዚህና መሰሎቻቸው፣ ምንም እንኳን እነሱ ቢያልፉም፣ ለአእምሮ ጅምናስቲክ ብለውም ይሁን ለሰው ልጅ አስበው የሰነዘሯቸው ሀሳቦችና እሳቤዎች ዛሬም ድረስ ብዙዎችን ያለ እንቅልፍ እያሳደሩ ይገኛሉ። በአካዳሚው ደብር ሳይቀር በእነሱ ላይ የሚካሄደው ውዝግብ ሌላ ነው። ባለቅኔው ጎሞራው (ኃይሉ) በ"በረከተ መርገም" የወረደባቸው "ውርጅብኝ" እንዲህ በቀላሉ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም።

እንደ አንዳንዶች፣ ዓለማችንን ከሚያዋክቧት ቀዳሚው የማህበራዊ ሳይንሱ ዘርፍ አካል የሆነው ፖለቲካ ነው። ድሮ ድሮ ኃይማኖት ነበር ቢባልም፤ ዛሬ እሱ ራሱ ተጠልፎ፣ በፖለቲካው ምህዋር ስር ሲሽከረከር እንጂ በነበረበት ሁኔታና አኳኋን ላይ ሆኖ እንኳን አይታይም። በግድ እንጠራጠር ካልተባለ በስተቀር እጅ ሰጥቷል። እንደውም፣ አንዳንዶች እንደሚሉት የኃይማኖትና ኃይማኖተኛነት ጉዳይ 18ኛው ክፍለ ዘመን ላይ "ቻው" ብሏል።

እርግጥ ነው የፖለቲካን ጉዳይ እዚህ እንዲህ ነው፤ እንዲያ ነው፤ እንዲህ አይደለም፣ እንዲያ አይደለም . . . በማለት የመጨረሻ ብያኔን ልንሰጠው እንቸገራለን። ለመቸገራችን ትልቁ ምክንያት ደግሞ መስኩ ሁሉም የሚሳፈረው ባቡር፤ ማንም የሚጋልበው ፈረስ የመሆኑ ጉዳይ ነው። በያኙም እንደዛው።

የዛሬዋ ዓለማችን ጉደኛ ነች። ለጉደኛነቷ ደግሞ ዋናው ምክንያት ዛሬ ማንም ተነስቶ ፖለቲከኛ የመሆን ሙሉ መብት አለው። ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት ካልሆነ በስተቀር "አልችልም" ብሎ ነገር የለም። እንደፈለገው ማድረግ፤ ያገኘው ላይ ሁሉ መፍረድ ዘመኑ የሚፈቅደው "ተራማጅ" አስተሳሰብ ነው።

ድሮ ጥልቅ እውቀት ወደ ፖለቲከኛነት ያመጣ ነበር ነው የሚባለው። ዛሬ በሀሰት ትርክት የትም መድረስ ይቻላል ነው የሚሉት የዚህ አስተሳሰብ አራማጆችና የእውነት ተቆርቋሪዎች። ድሮ መንደሬ፣ መንደሬ ማለት ያሳፍር ያልነበረውን ያህል ዛሬ አገሬ፣ አገሬ ማለት፣ ፅድቁ ቀርቶ . . . እንዲሉ፣ ሊያስጠይቅ ሁሉ ይችላል ሲሉ ምንም አያፍሩም፣ አይፈሩምም።

ዛሬ "መንገዶች ሁሉ ወደ ብሔር ይወስዳሉ" የተባለ ይመስል (በተለይ በአፍሪካ) ብሔር፣ ብሔር . . . ያለ፣ የብሔር (በእውቀቱ ሥዩም አንዳንድ ሰዎች "እግዚአብሔር" ከሚለው፣ እንዲመቻቸው አድርገው "እግዚአ"ን ገንጥለው በማስቀረት "ብሔር"ን ፈጠሩ ካለው ጋር ግንኙነት የለንም) ፖለቲካን ያቀነቀነ ምንም ቢሆን ፆሙን አያድርም ነው የሚባለው። አንድም አማራጭ የፖሊሲ ሰነድ እጁ ላይ ሳይኖር በ"ብሔሬ ተጨቆነ" ትርክት ብቻ የወንበርና መንበር ቁንጮ ላይ ፊጥ ማለትና መቶጀር የመቻሉን ጉዳይ "በአይናችን እያየን ነው" የሚሉ "ፉራ"ዎች ብዙ ናቸው። ናይጀሪያን ምሳሌ እየጠቀሱ፤ ወደ ደቡብ ሱዳን ጎራ እያሉ መረጃ እያጣቀሱ፤ የሶማሌውን የጎሳ ትርምስ "እነሆ በረከት" በማለት . . . "ቺርስ!!!" የሚሉ የመኖራቸውን ያህል፣ "ተከድኖ ይብሰል እንጂ የትም ያው ነው" ባዮችም ቁጥራቸው ከእነ"ቺርስ! " በላይ ነው።

ዓለምን ከሚገመግሙቱ፣ የቻይና ኮሚኒዝም ሀብት እንጂ መብትን አላጎናፀፈም፤ ከሚሉቱ ጀምሮ "የአሜሪካ ዲሞክራሲስ በአፍንጫዬ ይውጣ" እስከሚሉት ድረስ እስከሚዘልቁቱ ያሉት አስተያየቶች የትየለሌ ናቸው።

ከካፒታሊዝም/ኢምፔሪያሊዝም ጋር አይንና ናጫ የሆነውን ሶሻሊዝም/ኮሚኒዝም ለዓለማችን ብቸኛው አዋጭ (ረማጭ የሚሉት እንዳሉ ሆነው) የፖለቲካ ፍልስፍና ነው የሚል ክፍል የመኖሩን ያህል፤ አይደለም የእሱ ተቃራኒ የሆነውን ብቸኛው የዓለማችን መፍትሄ ነው የሚለውም በሽ በሽ ነው።

አንዳንዶች የድሮው (Mode of Production) ዘመነ ስልተ-ምርቶች (የጋርዮሽ፣ የባሪያ ፍንገላ፣ የፊውዳል እና የከበርቴ ስርዓቶች) በስንት ጣእሙ የሚሉ ናቸው። "ምክንያት" ሲባሉ፤ "ቢያንስ ቢያንስ በሰላም ወጥቶ መግባት፣ አብሮ መኖርን የሚከለክሉ አልነበሩምና" የሚለው አጭርና ግልፅ መልሳቸው ነው።

ደጋግመን እንዳልነው፣ ዓለማችን በተለያዩ ርእዮቶች ተወጥራ የተያዘች ነች። ሁሉም እንደየአቅሙና ፍላጎቱ የየራሱን ርእዮት ያራምዳልና ዓለማችን በአራቱም ማእዘን ብትወጠር የሚገርም አይሆንም።

ለመጀመሪያው ውጠራ ያችኑ አሜሪካንን በማሳያነት ሲያቀርቡ፤ ለሁለተኛው ውጠራ ደግሞ ሶቪየትንና ቻይናን በማስረጃነት ያቀርባሉ። እነዚህ፣ የሁለቱ ተቃራኒ የኢኮኖሚ ስርአቶች አራማጆች "የቱ ነው ትክክል?" ብለን እስከንጠይቅ ድረስ እያደናበሩን ያሉት ኃይላት፣ በተለይ ለአፍሪካ የሚጠቅማት ይሄ ነው፣ ይሄ ነው . . . በማለት (ያም ለኔ . . ያም ለኔ . . . እንዲል ድምፃዊው) መንታ መንገድ ላይ በመጣል በኩል እያደረሱት ያሉት ጥፋት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ቀዝቃዛው ጦርነት በዘመናዊ መልክ ተመልሶ የመጣ እስኪመስል ድረስ ምድር ቀውጢ ሆናለች።

ወደ አፍሪካችን ስንመጣ፣ ኮንጎ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ናይጀሪያ፣ . . . በምን ርእዮትና ፖለቲካዊ ፍልስፍና እንደሚመሩ እንኳን እኛ ራሳቸውም የሚያውቁት አይመስልም። አይኤስ (IS) እያተራመሳቸው ያሉትን አገራት ቤቱ ይቁጠራቸው።

የዶቸቬሌው ነጋሽ መሀመድና ባልደረባው ወቅታዊውን የሱማሊያ ጉዳይ በስፋት በዳሰሱበት ዝግጅታቸው "ከሰሜንና ሰሜን ምስራቅ የኤደን ባህረ ሰላጤን የተንተራሰችው፣ ከደቡብና ደቡብ ምስራቅ የህንድ ውቅያኖስን የረገጠችው ያቺን ሾጣጣ፣ ስልታዊ ሀገርን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ከወጣች ወዲህ አንድ አድርጎ ለመግዛት ብዙ ርእዮተ-ዓለምና ስልት ተሞክሮባታል። አብዲረሺድ አሊ ሸርማርኬ የምእራባዊያኑን፣ ዚያድባሬ ሶሻሊስታዊውን ርእዮተ ዓለም ገቢር አድርገውባታል። ጀነራል ፋራህ አይዲድ የጦር አበጋዝ አገዛዝን፣ ከአብዲ ቃሲም ሳላት አህመድ እስከ አብዱላሂ የሱፍ አህመድ የተፈራረቁት የጎሳ፣ የፖለቲካና የጦር አበጋዝ ስብጥር አስተዳደርን ሞክረውባታል። አልተሳካም።" በማለት ያለውን እውነታ ከነበሩት ሁኔታዎች ጋር አሰናስለው ይነግሩናል።

የርእዮተ ዓለም መጽሐፍ የሆነው "ማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገበ ቃላትም" "አፍሪካ ሶሻሊዝም (የ-)"ን በፈታበት ገጹ ላይ የሚያብራራውም የዚሁ ተመሳሳይ ሲሆን፣ ባጭሩ የአፍሪካ ችግር ወጥ የሆነ ርእዮተ ዓለም መከተል አለመቻልና በሶሻሊዝም ላይ ጥርት ያለ ሳይንሳዊ መሰረት ያለው ግንዛቤ አለመኖር ነው። ይህ ደግሞ እስከ አህጉራቱ ህብረት ጽሕፈት ቤት ድረስ የአሰራር ጉዳትን አስከትሏል።

እንደምናውቀው፣ እንደ ሞዴል የምናያቸው የአውሮፓ አገራት (ለምሳሌ ግራ ዘመም ሶሻል ዲሞክራሲ አራማጇ ጀርመን) እና የዲሞክራሲ ወላጅ አባት የምትባለው አሜሪካ "እምንልሽን ካልሰማሽ" በማለት ሩሲያን የውጥር ይዘዋታል። የፑቲን ንክች ያባ ቢላዋ ልጅ አቋም ነው እንጂ ያገዳቸው ዜሌንስኪንን የመታደጉን ስራ አጥብቀው ከያዙት ቆይተዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳያን በጦርነቱ እየተጎሳቆለች ያለችው ዓለማችን የትኛው ትክክል እንደ ሆነ ጠፍቷት መሀል መንገድ ላይ እየተናጠች መሆኗን ነው።

እያወራን ያለነው የቱ ትክክል እንደሆነና የትኛው ደግሞ ትክክል እንዳልሆነ ባለመለየት ስለመደናገራችን ቢሆንም፤ ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ መሆን ስላለመሆኑ ቢሆንም፣ በዓለማችን የርእዮት ግጭት (ideological conflict) መኖሩንም፤ መኖሩ ብቻ ሳይሆን አገራት ተቃራኒ ርእዮቶችን ሁሉ እያስተናገዱ ስለ መሆናቸውም መመልከት ያልተገደበ መብት አለንና እንቀጥል።

በተለይ ቀዝቃዛውን ጦርነት ተከትሎ አገራትን ጠቅልሎ በስር የመያዝ ፖሊሲን (containment ትለዋለች) የምትከተለው አሜሪካ በምንም መንገድ ሩሲያን በቁጥጥሯ ስር የማድረግ እቅድና ስልቷ ሊሳካላት ያልቻለ ሲሆን፤ ትንቅንቁ እስካሁንም ጋብ ሲል አልታየም። የሁለቱ በሁለት ጎራ መከፋፈልና መጠዛጠዝ አውሮፓዊያኑን ሳይቀር ለሁለት ጎራ (የአሜሪካ ተከታዮቹ Western European nations፤ የሩሲያን ጎራ የሚደግፉ Eastern European nations) እንዲከፈሉ ያደረገ ሲሆን ይህ ጎራ አሁንም በዚያው መንገድ ላይ ብቻ ሳይሆን ጥላውን አፍሪካ ድረስ እንዳጠላ ነው ያለው። ችግሩ እኛ ለእኛ የትኛው ትክክል እንደሆነ መለየት ባለመቻላችን ማእበል እንደሚያላጋው ግንድ እዚህና እዛ እየተላጋን እንገኛለን። በተለይ የእነዚህ ሁለት ኃያላን (አሁን በምእራባዊያኑ ብሎክ የማትወደደው፤ በአፍሪካ ተመራጭ የሆነችው ቻይና ተጨምራለች) በዚህ በአሁኑ ዘመንና ሰዓት እንኳን የእነሱ የርእዮት ግጭት ዓለምን ምን እያደረጋት እንደ ሆነ እያየንና እየሰማን ነው። አፍሪካም "ከእኔ ወይስ ከእሱ" ከሚለው የልጆች ጨዋታ ባልተናነሰ መልኩ "ምረጭ" ተብላ ስቃዩዋን እያየች ስለመሆኗ እኛ፣ የአሁኑ ዘመን ህያዋን ምስክሮች ነን። አሁን ወደ ውስጥ እንምጣ።

እዚህ እኛ አገር ይኑር አይኑር አይታወቅም፤ ወይም፣ ወደ 140 የሚሆኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች (በፈረንሳይ ከ1814–1815 ይፈሉ የነበሩትን የፖለቲካ ክበባት የሚያስታውስ) ነበሩ በሚባልበት ጊዜ እንኳን "ተቃዋሚ" ከሚለው በስተቀር እከሌ እንዲህ ነው ተብሎ የፖለቲካ አቋሙ (political outlook ወይም position) ሲገለፅ አይሰማም። ግልፅ የፖለቲካ አቋም እንደሚያራምዱት የአውስትራሊያው ዲሞክራት፤ ኢንዶኔዥያው ጎልካር (Golkar) ፓርቲዎች ማለት ነው። (ለነገሩ እኮ የእኛ አገር የፖለቲካ ፓርቲዎች ምንም አይነት "ኢዝም"፣ አንዳችም አይነት የፖለቲካ አቋም . . . የላቸውም ተብለው መታማት ከጀመሩ ጊዜው ቆይቷል። አማራጭ ፖሊሲ ሲጠየቁ እንኳን "እሱን ምረጡኝና እነግራችኋለሁ" ባዮች መሆናቸው ሲያስተቻቸው እንደ ነበር የሚረሳ አይደለም።

በአንድ ሰሞን የጋራ ውይይታቸው ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ለተቃዋሚ "ፖለቲካ ፓርቲዎች ጽሕፈት ቤት እንስጥ ብንል ኮንዶሚኒየምም አይበቃን" ያሉትን የረሳ ሰው ከዚህ ጽሑፍ ጋር በሚገባ ላይገባባ ቢችል ባይገርምም፣ ዛሬ እነዛ ሁሉ ፓርቲዎች እምጥ ይግቡ ስምጥ ግን የሚታወቅ ነገር የለም።

ሌላው የኛዎቹ የሚታሙበት ዋናው ነገር "ነጠላ ጉዳይ" (ምሁራት Single-issue politics ይሉታል) ላይ ብቻ መንጠልጠልና ማተኮራቸው ሲሆን፣ እሱም "ብሔር" እና በብሔር ዙሪያ ላይ ያጠነጠነ፤ የሕዝቡንም ፍላጎት መሰረት ያላደረገ (ያደረገ የሚሉት እንዳሉም ሳንረሳ - ቢያንስ ራሳቸው ስለሚሉት) መሆኑ እያስወቀሳቸው ይገኛል።

በግልፅ እንነጋገር ከተባለ የእኛ አገር ፖለቲካም ይሁን ፓርቲዎቹ ለግለሰብ ነፃነት ግድ የለሾች ናቸው። በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው፣ ሁሉም ፓርቲዎች ጉልበተኞች ናቸው። የገዥ/ተገዥው ሳያንስ "የተሻልን ነን" የሚሉት ሁሉ ከዛው መስመር የወጡ ስለመሆናቸው አንዳችም መተማመኛ የለም።

አወዳደቃቸውም ያውና ተመሳሳይ ሲሆን፣ እርስ በርሱ ተጠላልፎ እንዘጭ ማለቱ ላይ የሚያክላቸው የለም። ቅንጅት በለው ተመሳሳይ ነው። ሌሎቹ በመቶዎች የሚቆጠሩትም እርስ በርስ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን በልተው ነው ላይመለሱ የተጓዙት። ፖለቲካችን ሌላም ገጽታ አለው።

ባጠቃላይ፣ እኛ አገር፣ እንደ አንድ ጥንታዊትና ባለ ታሪክ አገር፣ አንድም እንኳን የወግ ጠባቂ (conservatism ("ወግ አጥባቂ"ነት ሳይሆን "ወግ ጠባቂ"ነት)) እሚሉት አልያም የእውነተኛ ዲሞክራሲ የፖለቲካ ርእዮት አራማጅ ፓርቲ አለመኖሩ ለብዙዎች ትንግርት ሲሆን፣ ሁሉን ነገር ዛሬውኑ ጥርግ አድርጌ ካልለወጥኩ የሚለው ስር ነቀላዊነት (Radicalism)፤ ከእሱ የባሰው አውዳሚነት (Nihilism) . . .፤ እንዲሁም ሌሎች ከማቆጥቆጥም ባለፈ እየተንሰራፉ መሆናቸው ለብዙዎች ራስ ምታት እንደሆነ ይገኛል። (ግን ግን፣ እንደው ለነገሩ፣ "ሰው በተፈጥሮው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው" (ጠቢቡ "Man is by nature a political animal" እንዳለው) ብለናልና፣ በአገራችን ከሚርመሰመሱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል "እኔ የምከተለው የፖለቲካ ርእዮት ይሄ ነው" ብሎ፣ ለይቶ የሚያውቅ፣ አውቆም ለተከታዮቹ (ለህዝብ መቼም አይታሰብም) የሚያስረዳ ፓርቲ አለ? "የምንከተለው ርእዮት ምንድን ነው?" ብሎ የሚጠይቅስ የፓርቲ አባል አለ? ወይስ፣ እንደው ምናልባት "መላ ካለው" በሚል፤ ወይም "ሰው በተፈጥሮው ፖለቲካዊ እንስሳ" ስለሆነ የተደራጀ ፓርቲና የታቀፉ አባላት ናቸው ያሉን? ያለ ርእዮተ ዓለም ትጥቅ ለውጥ አመጣለሁ ብሎ መፎከርንስ የፖለቲካ "ሀሁ"ም ሆነ አምላክ ይፈቅደዋልን?)

**ቸር እንሰንብት።**

# የዘመን ጥበብ

## ትንቢተ ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር››

**ዋለልኝ አየለ**




ስለፍቅር እስከ መቃብር የሚወራበት አጋጣሚ በጣም ብዙ ነው አንድ ማንበብ የማይወድ ሰው ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር ምንድነው?›› ተብሎ ቢጠየቅ ‹‹የሀዲስ አለማየሁ መጽሐፍ›› ብሎ መመለሱ አይቀርም ፍቅር እስከ መቃብርን ምንም ማንበብ የማይችሉ እንኳን ቢያንስ በስም ያውቁታል ምክንያቱም የሚሰማበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ

ምን እንደሆኑ ማብራራት አይችሉ ይሆናል እንጂ አረኞች እንኳን በዛብህና ሰብለ ወንጌል የሚባሉ እንዳሉ ያውቃሉ ከዚያ አለፍ ሲል ደግሞ ፊታውራሪ መሸሻና ጉዱ ካሳ የሚባሉ ሰዎች እንደነበሩ መጽሐፍ የማያነቡ ሁሉ ያውቃሉ እንዲያውም አሁን አሁን በዛብህና ሰብለወንጌል የሚባሉት በሕይወት የነበሩ ሰዎች የሚመስሏቸውም አሉ ይሄ ማለት የማያነቡና ልብወለድ መሆኑን የማያውቁ ሁሉ ስለፍቅር እስከ መቃብር ሰምተዋል ማለት ነው

ይህ የሆነው እንግዲህ በብዙ ምክንያት ነው አንደኛ ፍቅር እስከ መቃብር ከሰፈር ጨዋታ እስከ ትልልቅ መድረኮች ብዙ ተብሎለታል ከዚህም በላይ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ይደመጥ በነበረው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬዲዮ በ1990ዎቹ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተተርኳል ራሳቸው ሀዲስ አለማየሁ እንዳሉት ወጋየሁ ንጋቱ ለመጽሐፉ ሕይወት ሰጥቶታል በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ያሉ ገጸ ባህሪያት በሕይወት ያሉ እስከሚመስለን ድረስ ውስጣችን ገብተዋል የወጋየሁ ንጋቱ ትረካ ለማያነቡት ሁሉ መጽሐፉን እንዲታወቅ አድርጎታል

የማንበብና መጻፍ ልምድ ወደላቸው ሰዎች ስንመጣ ደግሞ ፍቅር እስከ መቃብር በርካታ ውይይቶች፣ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች ተደርገውበታል የቅድመ ምረቃም ሆነ የድህረ ምረቃ ምርምሮች ተሰርተውበታል በብዙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ዳሰሳ ተሰርቶበታል የሬዲዮና የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ላይ የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ብዙ ብለውበታል ብዙ የመድረክ ውይይት ተደርጎበታል

ፍቅር እስከ መቃብር ስሙ የሚነሳው ለሱ ተብሎ በተዘጋ መድረክ ላይ ብቻ አይደለም በየትኛውም የስነ ጽሑፍ መድረክ ላይ፣ የመጻሕፍት ውይይት ላይ ፍቅር እስከ መቃብር ስሙ ይነሳል የልብወለድ መጽሐፍ ማነጻጸሪያም ይደረጋል በማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥም ይጠቀሳል ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ቢያንስ በስም ያውቁታል

ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶችም በላይ ደግሞ መጽሐፉ በራሱ ላነበበው ሁሉ አይረሴ ሆነ እዚህ ጋ የበዛብህና ሰብለወንጌል ፍቅር አለ፤ እዚያ ጋ የቦጋለ መብራቱና የውድነሽ በጣሙ ፍቅር አለ፤ አሁንም እዚያ ጋ የፊታውራሪ መሸሻ እና ወይዘሮ ጥሩአይነት ፍቅር አለ የካሳ ዳምጤ እና የእንቆጳ ፍቅር አለ የሁሉም ፍቅር የሚሄደው እስከ መቃብር ነው ይህም በሰዎች ልብ ውስጥ አይረሴ አድርጎታል

ወዲህ ደግሞ በዚያ ዘመን የማይታሰበውን፣ በዚያ ዘመን ተደፍሮ የማይነገረውን ካሳ ዳምጤ(ጉዱ ካሳ) ደፍሮ እየተናገረ የአንባቢን ቀልብ ያንጠለጥላል እነ አበጀ በለው በዚያ በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ‹‹እምቢ!›› ማለት በማይታሰብበት ዘመን ‹‹አንገብርም›› እያሉ ያምጻሉ የመብት ጥያቄ ያነሳሉ ፍቅር እስከ መቃብር ፍቅር ነው፤ ፖለቲካ ነው፣ ማህበራዊ ሕይወት ነው መጽሐፉ በፍቅር፣ በማህበራዊ ኑሮ እና በፖለቲካ ብዙ ሊባልለት የሚገባ ነው

ይህን መጽሐፍ በሁሉም ዘውግ መዳሰስም ሆነ መወያየት ይከብዳል በፍቅር፣ በማህበራዊ ኑሮም ሆነ በፖለቲካ ሥርዓቱ እየለዩ ሊያወያይ ይችላል ከስነ ጽሑፍ ቅርጽ አንጻር ደግሞ ሌላ ራሱን የቻለ መድረክ መሆን ይችላል

ዛሬ ፍቅር እስከ መቃብርንና በፍቅር እስከ መቃብር ላይ የተባሉ ነገሮችን ማስታወስ የፈለግነው ሰሞኑን ፍቅር እስከ መቃብር አጀንዳ ስለሆነ ነው አንጋፋው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ፍቅርስ እስከ መቃብርን ለብዙዎች አስተዋውቋል እነሆ አሁን ደግሞ ዘመኑ በሚፈቅደው የዕይታ ቴክኖሎጂ በድራማ መልክ ሊታይ ነው ይህንንም የሚያደርገው አንጋፋው የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ነው ባለፉት ሳምንታት የተዋወቀ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ከባለሙያዎች ጋር ውይይት እየተደረገበት ነው

ድራማው ሲጀመር ምልከታችንን እና የባለሙያዎችን አስተያየቶች(ምናልባትም የመድረክ ውይይቶች ሊደረጉ ይችላሉ) እናያለን እስከዚያ ግን በተለያየ ጊዜ ስለፍቅር እስከ መቃብር በባለሙያዎች የተባሉትን እናስታውሳችሁ

በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ ይደረግ በነበረው የመጻሕፍት ውይይት ላይ ሚዩዚክ ሜይ ዴይ ከአምስት ዓመታት በፊት (የካቲት 11 ቀን 2010 ዓ.ም) በፍቅር እስከ መቃብር ላይ ውይይት አድርጎ ነበር በውይይቱም የስነ ጽሑፍ ባለሙያና መምህር መሰረት አበጀ ‹‹የግፍ መርህ ዳፋ- የሀዲስ አለማየሁ ደወል(በፍቅር እስከ መቃብር)›› በሚል በመነሻ ሀሳብ አቅርበው ውይይት ተደርጓል አቅራቢው ትኩረት ያደረጉት መጽሐፉ በፊውዳሉ የአገዛዝ ሥርዓት ላይ ብቻ ባለው ይዘት ነው ይሄውም በፊት ፊታውራሪ መሸሻና በነዋሪው መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ማለት ነው

በመጽሐፉ ውስጥ ፊታውራሪ መሸሻ የገዥው መደብ ወኪል ናቸው እርሳቸው የፊውዳሉን ሥርዓት ሲወክሉ ከጭቁኑ ሕዝብ ጋር የነበረውን ግብግብ ያሳያል የጭቁኑ ሕዝብ ጥያቄም የነጻነትና የፍትህ ጥያቄ ነው ይህም የግፍ አሰራር ነጻነትን በማሳጣቱ የመጣ ብሶት ነው የነበረው ጭቆና የተፈጥሮ መብትን ሁሉ የሚጋፋ ነው

በበዛብህና በሰብለወንጌል ፍቅር እንኳን ስንሄድ ሁለቱ እንዳይገናኙ ያደርጋል ግፍ ሲበዛ አመጽን ያስነሳል በዛብህና ሰብለወንጌል ግፍ ሲበዛባቸው አምጸዋል፤ ተሰደዋል በዛብህ ከወላጆቹ ኋላቀር እምነት ጋር፤ ሰብለወንጌልም ከወላጆቿ ኋላቀር አስተሳሰብና ልማድ ጋር፤ ጉዱ ካሳ ከሥርዓቱ አሮጌ አስተሳሰብ ጋር ሲፋለሙ ያሳያል ይሁን እንጂ የተናጠል እንቅስቃሴያቸው ደግሞ አሸናፊ አያደርጋቸውም የጉዱ ካሳ፣ የበዛብህና የሰብለወንጌል መጨረሻ ነጻነትና ፍትህ እንደናፈቁ መቅረት ይሆናል

ሌላኛው አይነት አመጽ ሕዝባዊ የሆነው ነው ይሄውም በገበሬዎችና በገዥው መደብ መካከል የነበረው ማለት ነው ቅራኔው በጣም የቆየ ነበር ይህንንም እነ አበጀ በለው አሳይተዋል

ፊታውራሪ መሸሻ ከተለመደው ግብር በተጨማሪ ለዓመት በዓል መታያ እንዲቀርብላቸው ፈለጉ ገበሬዎቹ ለሰላም ሲሉ ያቀርቡላቸው ነበር ፍትሃዊ እንዳልሆነ እያወቀ፤ ነገር ግን ሀብትና ንብረቱ እንዳይጠፋ፣ ልጆቹ እንዳይበተኑበት ሲል ገበሬው በደሉን እያወቀ ይገብር ነበር በኋላ ፊታውራሪ መሸሻ ግፉን በጣም ሲያበዙት ገበሬው ተሰብስቦ መመካከር ጀመረ ‹‹ግዴታ የለብንምና አንከፍልም›› አሉ ከመካከላቸውም አበጀ በለውን መረጡ ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ፊታውራሪ መሸሻ ፈተና የገጠማቸው እነ አበጀ በለው ዘመናዊ አስተሳሰብ የነበራቸው ሆኑ አበጀ በለው ፊታውራሪ መሸሻን በማረካቸው ጊዜ ‹‹ተዋግተህ እንኳን ብትይዘኝ አይቆጨኝም ነበር›› ሲሉት ‹‹ተዋግቼ መያዝ እችል ነበር፤ ግን እኔ ደም እንዲፈስ አልፈልግም›› ነው ያላቸው

‹‹ገበሬ እና ወይፈን እንዛዝላ ሲጥሉበት ነው›› ይሉ ነበር ፊታውራሪ መሸሻ ገበሬን ከከብት ጋር እያነጻጸሩ ማለት ነው ገበሬውን እንዲህ ሲንቁ ሲንቁ ነው ኋላ ጉድ የሰራቸው ፊታ ውራሪ መሸሻ ገበሬዎችን ለመያዝና ለመቅጣት ሲዘምቱባቸው ገበሬዎች ግን ይሸሹላቸው ነበር፤ ይህም ደም እንዳይፈስ በማሰብ ነው ፊታውራሪ ግን ይህን አልተረጎሙትም፤ ፈርተውኝ ነው የሚሸሹ ብለው ነው ያመኑት ከእርሳቸው ይልቅ ሕዝቡ ሰላም ይፈልግ ነበር ማለት ነው ከዘመኑ አስተሳሰብ ወጣ ያለ ዕይታ የነበረው ጉዱ ካሳ ‹‹ልጅ ናቸው፤ አያውቁትም›› እያለ ይሳለቅባቸው ነበር አበጀ በለው ደግሞ ‹‹ህጋዊ ሽፍታ›› ይላቸው ነበር

ፊታውራሪ መሸሻ በእኩልነት አያምኑም በዛብህን ‹‹የድሃ ልጅ›› እያሉ የባላባት ልጅ ባለመሆኑ በጣም ያሳንሱታል ልጃቸው ሰብለወንጌል ‹‹እርስዎ የድሃ ልጅ የሚሉትን እኔ እወደዋለሁ›› ስትላቸው ‹‹ያ መተተኛ የተበተበብሽ መተት ነው እንዲህ የሚያደርግሽ›› እያሉ ይቆጣሉ ምክንያቱም ራሳቸውን የተቀባ የባላባት ዘር አድርገው ስለሚያስቡ ሌላውን አሳንሰው ነው የሚያዩት

ፊታውራሪ መሸሻ እምነታቸውም የተምታታ ነው ዳዊት ይደግማሉ፣ ልጃቸውንም ያስተምራሉ፣ ጊዮርጊስን ያምናሉ፤ ያስቀድሳሉ ይሁን እንጂ ከባዕድ አምልኮ የተላቀቁ አይደሉም ዘመቻ ሲሄዱ ቀበሮ ካገኙ እንደ መጥፎ ዕድል ነው የሚቆጥሩት ጊዮርጊስን እያመኑ ያሰቡት ነገር ካልደረሰላቸው ደግሞ ‹‹ጊዮርጊስ ከዳኝ›› እያሉ ይወቅሱታል ፈረሳቸውን እንኳን ‹‹እንደ ጊዮርጊስ እንዳትከዳኝ›› ብለውታል

ፊታውራሪ መሸሻ ያንን ሁሉ ግፍ ይዘው መጨረሻ ላይ ግን ተሸንፈዋል ልጆቻቸው ተሰቃይተዋል፣ ራሳቸው ተሰቃይተዋል፣ ከብቶታቸውን ተዘርፈዋል የገዢው መደብ ወካይ ነበሩና የሥርዓቱን ውድቀት አሳይተዋል ፍትህ ለማግኘት ሲደክሙም አድካሚነቱን አይተዋል

የስነ ጽሑፍ ባለሙያና መምህሩ መሰረት አበጀ እንደሚሉት፤ ስነ ጽሑፍ መጻፍ ያለበት መሆን ስለሚገባው ቅንና በጎ ጉዳይ ነው ስለመከባበር ማሳየት አለበት መጥፎውን ነገር ብቻ መጻፍ ከገሃዱ ዓለም ከሚታየው የተለየ አይሆንም በአገራችን ግን የማንበብ እንጂ የመተርጎም ችግር እንዳለ ያሳያሉ ለዚህም አንድ ምሳሌ ይጠቅሳሉ በዓሉ ግርማ ‹‹የቀይ ኮከብ ጥሪ›› መጽሐፉ ላይ በጣም መመስገን ነበረበት፤ ግን ብዙም ሲመሰገንበት አይሰማም እንዲያውም የመንግስት ደጋፊ ተደርጎ ነበር የተወሰደው በቀይ ኮከብ ጥሪ ላይ ግን ደርግና ኢህአፓ መታረቅ እንዳለባቸው ነው ያሳየው ሌላ መንግስት ከሚመጣ ያለውን መንግስት ማረቅና ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ነው የገለጸው

ሂሩት ኢህአፓ ናት ደርቤ ደግሞ የአብዮት ጠባቂ ነው ሂሩት ተመታ ስትወድቅ ደርቤ አንስቶ ወደ ሆስፒታል ይወስዳታል የዚህም መልዕክት ኢህአፓና ደርግ እንዲታረቁ ነው

ፍቅር እስከ መቃብር ለውጥ ፈላጊነትን ያሳያል ግፍ መጨረሻው እንደማያምር ያሳያል ድርሰቱ በወቅቱ የነበረው የዘውዳዊ አገዛዝ የአንድ ብሔር የበላይነት የሚታይበት እንዳልሆነም ያሳያል የገዥው መደብ ወካይ ፊታውራሪ መሻሻ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ናቸው ፍዳ ሲያሳዩት የነበረው የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪውንና የክርስትና እምነት ተከታዩን ነበር፤ የራሳቸው ወገን ላይ ነው ያን ሁሉ ግፍ ሲፈጽም የነበረው

ደራሲው ሀዲስ አለማየሁ በፊታውራሪ መሸሻ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን አገዛዝ ነው ያሳዩት እንግዲህ እዚህ ላይ ነበር ከመድረኩ ተሳታፊዎች አንድ ክርክር የተነሳው ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሀዲስ አለማየሁን ሸልመዋቸዋል ጥያቄ የሆነው ‹‹የእርሳቸው አገዛዝ የግፍ አገዛዝ መሆኑን እየተረከ እንዴት ሊሸልሙ ቻሉ?›› የሚለው ነው አንዳንዶቹ ‹‹ንጉሱ መጽሐፉን ሳያነቡት ይሆናል፤ ወይም አልገባቸውም ማለት ነው›› ብለዋል አንዳንዶቹ ደግሞ ‹‹የለም! እንዲህ ማለትማ ድፍረት ነው፤ እንዴት አያነቡትም? እንዴትስ አይገባቸውም? በቃ! ሥራው ድንቅ ስለሆነ ተደስተውበት ነው፤ እንዲያውም ንጉሡ በቤተ መንግሥት ውስጥ ከነበሯቸው መጻሕፍት አንዱ ፍቅር እስከ መቃብር ነበር›› ብለዋል

የስነ ጽሑፍ ባለሙያና መምህር መሰረት እንደሚሉት፤ በወቅቱ በስነ ጽሑፍ መዝነው ሽልማት የሚሰጡት የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ነበሩ ንጉሡም ያንን አይቃወሙም ቢያነቡትም ባያነቡትም የመጽሐፉን ታሪክ ያውቁታል መሪዎች በፖለቲካም፣ በኢኮኖሚም በየትኛውም ነገር አስረጂዎች አሏቸው ባለሙያዎች ይነግሯቸዋል ዳሩ ግን ንጉሡ ለምን ሀዲስ አለማየሁን እንደሸለሙ ተጠይቀው ‹‹እንደዚህ መሆኑን እኔ መቼ አውቄ›› ብለዋል በዚያ ላይ በወቅቱ የነበራቸው ጊዜ ያንን መጽሐፍ ለማጣጣም የሚያመች አልነበረም በፖለቲካ ሥራ ተጠምደው ነው የሚውሉት

ፍቅር እስከ መቃብር እውነትም የዘመኑን ዘውዳዊ አገዛዝ የተነበየ ነበር ማለት ነው የሥርዓቱ ወካይ ፊታውራሪ መሸሻ መጨረሻቸው እንዳላማረው ሁሉ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መጨረሻም አላማረም የነበረው የባላባትነት ዘመን አክትሟል በባላባትነት ያምኑ የነበሩት ንጉሱ በመጨረሻ በደርግ እጅ ገብተዋል ሥርዓታቸው መውደቅ ብቻ ሳይሆን እርሳቸውም ተሰቃይተዋል

በነገራችን ላይ የስነ ጽሑፍ ባለሙያና መምህር መሰረት ከተናገሩት ‹‹ትርጉም›› የሚባለው ነገር ልብ ሊባል ይገባል ብዙዎቻችን እናነባለን እንጂ አንተረጉምም ለዚህም ነው አረዳዳችን የተለያየ የሚሆነው እርግጥ ነው ቢተረጎምም ልዩነት ሊኖር ይችላል፤ የተለያየ አተረጓጎም ይኖራል

ለምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብርን ያነበበ አንድ ወጣት፣ አንድ የሃይማኖት እና አንድ ፖለቲከኛ ስለመጽሐፉ ጭብጥ ብንጠይቅ የተለያየ አረዳድ ልናገኝ እንችላለን ምናልባትም ወጣቱ ስለ በዛብህና ሰብለወንጌል የፍቅር ጽናት፣ የሃይማኖት አባቱም ስለ እምነት፣ ፖለቲከኛውም በዘውዳዊ ሥርዓቱ ውስጥ የነበረውን አገዛዝ ሊነግሩን ይችላሉ መጽሐፉ ከዚህም በላይ ብዙ የሚያወያይ ነው

እነሆ አሁን ደግሞ በቴሌቭዥን ድራማ ሊመጣ ነው፤ ተጨማሪ ሀሳቦችና ዕይታዎች ይንሸራሸራሉ ዘመን ተሻጋሪ ሥራ እንዲህ ሕያው ይሆናል!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ንቀትና ጥቃት ያማረራቸው የአካል ጉዳተኛ

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት እኔም ሙሉ አካል ነበረኝ።በሬ ጠምጄ የቤተሰቦቼን እርሻ ማርስም ጎበዝ ነበርኩ።ያኔ በተወለድኩበትም ሆነ በየትኛውም ሥፍራ ክብር ሲሰጠኝ ቆይቷል።እግር ነበረኝና እንደ ዛሬ የሚንቀኝና የሚያጠቃኝም አልነበረም ›› ይሄን ምሬትና ቁጭት አዘል አስተያየት የሰጡን ቅድስተ ማርያም አካባቢ ያገኘናቸው መሪ ጌታ ታሪኩ አበበ ናቸው።

ደጋግመው ‹‹ሙሉ አካል ያስከብራል›› የሚሉት መሪ ጌታ ታሪኩ እንዳጫወቱን ተወልደው ያደጉት መርሀ ቤቴ ደራ ከተማ ነው።ከሰባት ዓመት በፊት ታዲያ በገጠር ቀመሷ ደራ ከተማ ውስጥ በሙሉ አካላቸው ሲንቀሳቀሱ ኖረዋል።ሁሉም የሰውነታቸው ክፍል ምንም ችግር ያልነበረበት ጤናማም ነበሩ።በሬ ጠምደውም ከአሥር ገዝም በላይ የቤተሰቦቻቸውን እርሻም አገላብጠው የሚያርሱ ጎልማሳ ነበሩ።በቤተ ክህነት ትምህርት ከፊደል ጀምረው እስከ መሪ ጌታ የደረሰ ዕውቀት በመቅሰማቸውም በአካባቢያቸው በነበረው የደራ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ለዓመታት በድቁናም እያገለገሉ ቆይተዋል።ሙሉ አካል በነበራቸው ጊዜ በዚሁ በቤተ ክህነት የተማሩትን ዜማና ግጥም መሰረት ያደረገ የቅዳሴ ስነስርዓት ትምህርት መሰረት አድርገውም ይቀድሱም ነበር።ታዲያ ያኔ ክብር ነበራቸው።ብዙ የሚያውቋቸው ሰዎች ሰላምታ ሲሰጧቸው እንኳን እጥፍ ዘርጋ ብለው ነበር።በየትኛውም ሥራ ለመሳተፍም ቀዳሚው ተመራጭ እሳቸው ነበሩ።ከእርሻና ከቤክርስቲያን ግልጋሎት ውጪ ጠመንጃቸውን ይዘው ጎምለል ጎምለል ዞር ዞር በማለት አካባቢያቸውን የሚጠብቁ ተፈሪም ነበሩ፡፡

የዛሬ ሰባት ዓመት ግን ይሄን ክብራቸውን የገፈፈ አደጋ ገጠማቸው።እራሳቸውንና አካባቢያቸውን የሚጠብቁበት ጠመንጃቸው እንዳይቆሸሸ ሁሌም እንደሚያደርጉት እየወለወሉ ነበር።የሚወለውሉት ላያቸው ላይ አስቀምጠው ነው።በሚወለውሉበት ሰዓት ጥይት መውጫ አፈ ሙዙ ታፋቸው ስር ነበርና ጠመንጃው ባርቆ የግራ ታፋቸውን


መሪ ጌታ ታሪኩ አበበ

ገንጥሎ ጣላቸው። በዚህ ምንክንያት አካል ጉዳተኛ ሆኑ።ግን በአካላቸው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት እንደበፊቱ ሥራ ለመሥራት አልቻሉም።ቤተክህነትም በቀድሞ አገልግሎታቸው ልታስቀጥላቸው አልቻለችም።ምንም እንኳን አካል ጉዳተኝነት ስራን ባይከለክልም በሕብረተሰቡ ውስጥ የነበረው የተዛባ አመለካከት ሥራ ሰርተው ራሳቸውን ማስተዳደር እንዳይችሉ አደረጋቸው ‹‹እንዲህ ሆኜ የተወለድኩበትና ያደግኩበት አካባቢ አልኖርም›› በማለትም ጊዜ ሳያጠፉ ፈጥነው ወደ አዲስ አበባ መጡ።አዲስ አበባም ቢሆን ሕብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኛ ያለው አመለካከት የበለጠ የተዛባ በመሆኑ መፍትሄ እንዳልሆናቸውም አቶ ታሪኩ ይናገራሉ።

"እዚህ ከመጣሁ ጭራሽ ክብሬንም በአካሌ ጉዳት ምክንያት የተገፋፍኩ እስኪመስለኝ ድረስ ጥቃትና ንቀት ደረሰብኝ›› ሲሉም ይናገራሉ።እንደሚሉት አዲስ አበባ የመጡት የዛሬ ሰባት ዓመት አደጋው እንደረሰባቸው ነው።ታዲያ ያኔ መጠለያም አልነበራቸውምና በጣም ተቸግረዋል።ውሎ ሲያድር ጃን ሜዳ መግቢያ አካባቢ ያሉ የመከላከያ አባላት እዛው አካባቢ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሆነች ልታስጠልላቸው የምትችል ተንቀሳቃሽ ቤት ተጋግዘው ሠሩላቸው።በዚህች ቤት ውስጥ እየኖሩም በአቅማቸው የዕለት ጉርሳቸውን የሚሸፍን ሥራ ማፈላለጉን ተያያዙት።ግን ደግሞ በአቅሜ ልሰራ የምችለውን ዘበኝነት እንኳን ቅጠሩኝ ብለው የጠየቋቸው ብዙ ሰዎች ሳቁበቸው።ተሳለቁባቸው።ሌላው ቀርቶ ሲቀድሱበት በነበረው የቤተክህነት ሙያቸው በሰበካ አስተምሮት ለማገልገልም አራት ኪሎ መንበረ ፓትሪያክ መቀመጫ በሆነችው ቅድስተ ማርያም ገዳምም ጠይቀዋል።ሆኖም በአካላቸው ጉዳት ምክንያት ሥራ መቀጠር በቀላሉ አልሆነላቸውም።ግን ደግሞ በወቅቱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት የሠሩላቸው ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት በአገልግሎት ብዛት አርጅቶና ወላልቆ ነበርና ሥራው ይሄንንም ለማደስ የሚያስችል ገቢ ለማግኘት ስለሚያስፈልጋቸው ብዙ ሲደክሙ ቆይተዋል።

ያም ሆነ ይህ ከዛው ከቅድስተ ማርያም አካባቢ ሳይጠፉ ጧፍና ሻማ ሲያገኙ በመሸጥም ሲያጡም ከአገራቸው ቋጥረው የመጡትን ገንዘብ በመብላት እንዲሁም የቆርቆሮ ቤታቸውን በማሳደስ ዓመታት ሲያስቆጥሩ ቆዩ።ታዲያ አንድ ዕለት በዚያው በቅድስተ ማርያም ገዳም አካባቢ ታላቋ የዓለም የሰው ዘር ቅሪት ሉሲ የምትገኝበትን ሙዚየም ተደግፈው ከነዊልቸራቸው ቁጭ እንዳሉ ፍሬን የተበጠሰበት መኪናም እላያቸው ላይ ሊወጣ ሲል ነፍስ ይዟቸው ዘለው በመነሳት ብረቱ ላይ በመንጠልጠል ድነዋል።ቁጭ ባሉበት የገጠማቸውና ሕይወታቸውን የተፈታተነ አደጋ ይሄ ብቻ አልነበረም።አንዱ አሽከርካሪ ከነውልቸራቸው በአንድ ጎናቸው ይገጫቸዋል። የገጫቸውም አካላቸው በመጎዳቱ ብዙም ጥንቃቄ ሊያደርግ በማያስችለው ንቀት ነበር።እንዲህም ሆኖ በአንድ በኩል ያለው ዊልቸራቸው በመጎዳቱ ከእሳቸው ይልቅ እግራቸውን ተክቶ ከወዲያ ወዲህ የሚያንቀሳቅሳቸውን ዊልቸር ነበርና ያሳሰባቸው እንዲያስሩላቸው ይጠይቁታል።ሆኖም አሽከርካሪው በጀ አላለም በንቀት እያየ ጭራሽ አሾፈባቸው።መኪና ውስጥ ገብቶም ሊሄድ ሲሞክር ትዕግስታቸው ከልክ በማለፉ አጠገባቸው ተቀምጦ በነበረው አንድ አካል ጉዳተኛ ክራንች የሰውየውን መኪና መስትዋት በሁሉም በኩል አደቀቁት።ወንጀለኛ ተብለውም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰዱ።ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የታሰሩበት ቦታ የነበረው መፀዳጃ ዳገታማ በመሆኑ ለእሳቸው አይመችም ነበር።ታዲያ ይህንን በትህትና አሳወቁ።ሆኖም የሚሰማቸው አላገኙም።ከዚህ ሁሉ በመነሳት መሪ ጌታ ሕብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኛ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት ጉዳተኛውን ይበልጥ የሚያጠቃና የሚያስንቅ ወይም ዝቅ አድርጎ የማየት እንደሆነም ያወሳሉ።"ይሄን የምለው ዝም ብዬ እና ከመሬት ተነስቼ ሳይሆን በራሴ ከደረሰብኝ በመነሳት ነው››ይላሉ።ፍላጎቱ ቢኖራቸውም ሊያሰራቸው የሚችል ሰው አለማግኘታቸውንም እንደ ምክንያት ያቀርባሉ።ማንኛውም በአካል ጉዳተኞች ዙርያ የሚደረግ ድጋፍ ሁሉንም አካል ጉዳተኞች ተደራሽ ማድረግ አለበት የሚል ሀሳብም አዘውትረው ሲያንፀባርቁ ይደመጣሉ፡፡

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የአካል ጉዳተኞችና አድቮኬሲ ዴስክ ቡድን አስተባባሪ አቶ ሲሳይ ጥላሁን ሕብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኞች ያለው አመለካከት በአካል ጉዳተኞች ላይ ተደራቢ ችግር የሚፈጥር መሆኑን ይናገራሉ።አሁንም አመለካከቱ ሙሉ በሙሉ አለመቀረፉንና ለመቅረፍ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መገኘታቸውንም ያወሳሉ።እንደ አገር የሚደረገውም ድጋፍ ሁሉንም የአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲያደርግ እየተሰራ መሆኑን ያነሳሉ።

# ዓለም አቀፍ



## ሞዛምቢክ በአደገኛ አውሎ ንፋስ ዳግም ልትመታ እንደምትችል ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከመጋቢት ወር መጀመሪያ አንስቶ ሞዛምቢክ በአደገኛ አውሎ ንፋስ ዳግም ልትመታ እንደምትችል ተገለጸ።

ፍሬዲ የሚል ስም የተሰጠው ይህ አውሎ ንፋስ ባለፈው ሰኞ ማዳጋስካርን የመታ ኃያል አውሎ ንፋስ መሆኑንና ሞዛምቢክንም ሊያጠቃ እንደሚችል ቢቢሲ የአየር ትንበያ ባለሙያዎችን ዋቢ አድርጎ ዘግቧል።

የማዳጋስካር መንግሥት እንዳለው በዚህ አውሎ ንፋስ ስምንት ሰዎች ሲሞቱ አንድ ሺህ የሚጠጉት ቤት አልባ ሆነዋል።

አውሎ ንፋሱ አደጋ ማድረስ የጀመረው በደቡብ ምሥራቅ አፍሪካ በየካቲት ወር አካባቢ ሲሆን፤ በሁለቱ አገራት በድምሩ 21 ሰዎችን ገድሏል፤ ሺዎችን አፈናቅሏል።

የአየር ትንበያ አዋቂዎች እንደሚሉት ይህ የትሮፒካል አውሎ ንፋስ የአቅጣጫ ለውጥ የማድረጉ ነገር እምብዛምም የተለመደ አይደለም።

የትሮፒካል አውሎ ንፋስ በታሪክ ረዥም ጊዜ የዘለቀ አውሎ ንፋስ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በየጊዜውም ግፊቱን እየጨመረ ነው የመጣው። አውሎ ንፋሱ ሕንድ ውቅያኖስን ይዞ 8ሺህ ኪሎ ሜትር ተጉዟል።

ይህ ፍጥነቱ የብዙ የአየር ትንበያ ባለሙያዎችን ትኩረት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲስብ አድርጎታል።

አውሎ ንፋሱ መነሻውን ያደረገው በሰሜን አውስትራሊያ ጠረፍ በየካቲት ወር ሲሆን ከዚያ በኋላ በሺህ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ በደቡባዊ የሕንድ ውቅያኖስ አድርጎ ሞሪሽየስ ላይ ጉዳት አድርሶ ከሁለት ሳምንት በፊት ማዳጋስካር ደርሷል።

ቀጥሎ ደግሞ በሞዛምቢክ ጉዳት እንደሚያደርስ የዓለም አቀፉ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲና የዘርፉ ባለሙያዎች ገልጸዋል።

የአንድ አውሎ ንፋስ በተወሰነ ጊዜ ያለው ጉልበት ሲሰላ የትሮፒካል አውሎ ንፋስ ከባድ ክምችትና ጉልበት ያለው ሆኖ በክብረ ወሰን መመዝገቡ ታውቋል።

ማዳጋስካር ባለፈው ሳምንት በወር ታገኝ የነበረውን አማካይ የዝናብ መጠን ሦስት እጥፍ አግኝታለች። ይህም ከአውሎ ንፋሱ ጋር የተያያዘ ነው ተብሏል።

የተባበሩት መንግሥታት ያልተለመዱ የአየር ንብረት ለውጦችን የሚገመግመው ኮሚቴ አውሎ ንፋሱ ካለፈ በኋላ በጉዳዩ ላይ ጥናት እንደሚያደርግ ይጠበቃል ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ምዕራባውያን ተመራማሪዎች የቻይና የሰው የዘረ-መል ማሻሻያ ሙከራ ግልጽነት እንደሚጎድለው አሳወቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ምዕራባውያን ተመራማሪዎች በቻይና የሚደረጉ የሰው ልጆች ላይ የዘረ-መል ማሻሻያዎች ለማድረግ የሚደረጉ ጥናቶች ግልጽነት ስለሚጎድላቸው አሳሳቢ መሆናቸውን አስታወቁ።

የቻይና መንግሥት የዘረ-መል ማሻሻያ ምርምርን በተመለከተ ያለው ሕግ በተለይ በግል ኩባንያዎች ሊጣሱ የሚችሉ ናቸው ሲሉ ምዕራባውያን ተመራማሪዎች ስጋታቸውን መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ቻይና ግን በቅርቡ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚ ያደረገችው መመሪያ ዓለም አቀፍ ሕግጋትን የተከተለ መሆኑን አመልክተው፤ ሙያዊ ሥነ-ምግባር ማረጋገጥ፣ ቁጥር እና ፍተሻ ማድረግ የሚያስችል ነው ስትል የምዕራባውያን ተመራማሪዎችን ስጋት ታጣጥላለች።

የሰው ልጆች ላይ የዘረ-መል ለውጥ በማድረግ ወደ ልጆች ሊተላለፍ የሚችል በሽታ ለይቶ ማውጣት እንደሚቻል ተመራማሪዎች ያምናሉ።

ይሁን እንጂ የዘረ-መል ማሻሻያ ማድረግ አግባብነት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የለውም። አንዳንዶች ይህ ቴክኒክ ከልጅ ልጅ የሚተላለፍ ቋሚ የዘረ-መል ለውጥ በማምጣት የአንድን ሰው ልዩ መለያ ሊያሳጣ ይችላል ሲሉም ይከራከራሉ።

መቀመጫውን በዩናይትድ ኪንግደም ያደረገው ክሪክ ኢንስቲትዩት የተባለው ባዮሜዲካል ምርምር ተቋም፣ ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ሮቢን ሎቬል-ባጅ በቻይና የምርምር ሥራዎች ግልጽ የማይደረጉ ነገሮች ስላሉ ነገሩ አሳሳቢ ነው ይላሉ።

ቻይና በቴክሎጂው ቀዳሚ መሆን ለምን እንደምትፈልግ ይገባኛል፤ ነገር ግን አንዳንድ ዘርፎች



ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ፤ ከእነዚህ መካከል አንዱ የዘረ-መል ለውጥ ምርምር ነው ብለዋል።

ይህ ሙከራ አግባብ በሆነ አስተዳደር እና ክትትል ስር መካሄድ አለበት። ይህን እያደረጉ ስላልሆነ ስጋት አለኝ ሲሉ መናገራቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

በካናዳ ዳልሆስ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ፍንኮስ ባይሊስ በበኩላቸው በቻይና የሚደረጉ የዘረ-መል ለውጥ ምርምሮች ክትትል ብቻ ሳይሆን ባለሙያዎቹ ሙያዊ ሥነ-ምግባር የተላበሱ መሆን አለባቸው ይላሉ።

ተመራማሪዋ በቻይና ብቻ ሳይሆን በሰሜን አሜሪካ ያሉ የግል ኩባንያዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ትልቅ ፈተና መሆኑን ይናገራሉ።

ከቻይና አካዳሚ ኦፍ ሳይንስ የተወከሉት ዶክተር ያንጊን ፔንግ ግን መንግሥታቸው የዘረ-መል ምርምር መመሪያዎችን እና ሕጎችን ጥብቅ ማድረጉን ይገልጻሉ።

# ስፖርት



## የዓለም አትሌቲክስ በ2023 የፆታ እኩልነት ላይ ትልቅ ርምጃ ይወስዳል

**ቦጋለ አበበ**

የዓለም አትሌቲክስ በተያዘው 2023 የውድድር አመት ከፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ በርካታ ርምጃዎችን በመውሰድ የተለያዩ ለውጦችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ገልጿል። ከነዚህ ርምጃዎች መካከል የዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት ውስጥ ሴቶች አርባ በመቶ መቀመጫ እንዲኖራቸው ማድረግ አንዱ ሲሆን ከነዚህ ውስጥም ቢያንስ አንድ ሴት ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲኖር ይደረጋል ተብሏል።

በዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት ሴቶች አርባ በመቶ መቀመጫ እንዲኖራቸው ለተጀመረው ጥረትም ስፖርቱን ይመራሉ ተብለው ለሚጠበቁ ሴቶች ከወዲሁ የተለያዩ አስተዳደራዊ ስልጠናዎች በበይነ መረብ እየተሰጠ ይገኛል። ይህንንም የዓለም አትሌቲክስ 214 አባል አገራት 2023 መጨረሻ ድረስ ተግባራዊ እንዲያደርጉ አቅጣጫ ተቀምጧል።

የዓለም አትሌቲክስ በስፖርቱ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ እወስዳለሁ ያለውን ርምጃ በይፋ የገለጸው ትናንት የተከበረውን ዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን አስመልክቶ ሲሆን፣ ፕሬዝዳንቱ ሴባስቲያን ኮ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው ባስተላለፉት መልእክት " የዓለም አትሌቲክስ በስፖርቱ የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ቀዳሚ ሆኖ የተለያዩ ርምጃዎችን እንደሚወስድ ይፋ ማድረጉን ስገልፅ ኩራት ይሰማኛል" ያሉ ሲሆን ይህ ርምጃ የዓለም አትሌቲክስ እኤአ በ2016 ተቋማዊ ሪፎርም ለማድረግ ካስቀመጣቸው ግቦች አንዱ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኮ በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመገናኛ ብዙሃን እንደገለፁት፣ በዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት በአሁኑ ወቅት ሴቶች ስምንት ውክልና ብቻ ነው ያላቸው። ይህንን ቁጥር በ2023 ነሐሴ ላይ በሚካሄደው ምርጫ ላይ ወደ አስር ለማሳደግ የታሰበ ሲሆን አንድ ሴት ምክትል ፕሬዝዳንትም እንዲኖር ይደረጋል። ይህም በምክር ቤቱ የሴቶችን ቁጥር አርባ በመቶ ያሳድገዋል ተብሎ ይጠበቃል። የዓለም አትሌቲክስ ሴቶች በአስተዳደራዊ ስልጣን ሃምሳ በመቶ ቦታ እንዲኖራቸውም እኤአ እስከ 2027 ጥረቱ እንደሚቀጥል የፕሬዝዳንቱ ማብራሪያ ይጠቁማል።

ከአስተዳደራዊ ጉዳዮች ባሻገርም ዓለም አቀፉ ተቋም ከፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ የተለያዩ ርምጃዎችን የሚወስድ ሲሆን የሴት አሰልጣኞች ጉዳይ አንዱ ነው። በዚህም በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች የሴት አሰልጣኞችን ቁጥር ቢያንስ ሃያ በመቶ እንዲደርስ ታስቧል። ይህም እኤአ በ2025 የቶኪዮ የዓለም ቻምፒዮና ተግባራዊ ለማድረግ የታሰበ ሲሆን አባል አገራትም ተግባራዊ እንዲያደርጉ ዓለም አቀፉ ተቋም የተለያዩ ማበረታቻዎችንና ድጋፎችን እንደሚያደርግ አሳውቋል። ለዚህም የዓለም አትሌቲክስ ከተባበሩት መንግስታትና የዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋር በመተባበር የሴት አሰልጣኞችን ቁጥር ወደ አርባ በመቶ የማሳደግ ግብ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ሴት አትሌቶች በተለይም በጎዳና ላይ ውድድሮች የተሻለ እድልና እኩል የሽልማት መጠን እንዲያገኙም ከተለያዩ የውድድር አዘጋጆች ጋር በቅርበት እየተሰራ መሆኑን የገለፁት ኮ፣ ሴት የውድድር ዳኞችን የተመለከተ በርካታ ስራ እንደሚሰራም አብራርተዋል።

በተለያዩ የዓለም መገናኛ ብዙሃን ከአትሌቲክስ ጋር በተገናኘ ሴት አትሌቶች ውክልና እንዲኖራቸው ዓለም አቀፉ ተቋም ጥናቶችን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተጠቁሟል።

"በምንኖርባት ዓለም ለሴቶች እኩል እድልን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት በቂ አይደለም፣ እኛ ይህን እኩልነት ቀዳሚ ሆነን ለማረጋገጥ የግድ ጥረት ማድረግ አለብን፣ እውነተኛ እኩልነትን በስፖርታችን እውን ማድረግ አለብን፣ ሴት አትሌቶቻችን፣ አሰልጣኞቻችን፣ ዳኞቻችንና አመራሮቻችን በሁሉም መስክ እኩል ሆነው ራሳቸውን የሚያሳዩባቸው የተመቻቹ ሁኔታዎችን ልንፈጥርላቸው ይገባል፣ ለሌሎች የስፖርት ተቋማትም በዚህ ተግባር ምሳሌ መሆን እንችላለን" ያሉት ኮ፣ ሴት አትሌቶችንና ባለሙያዎችን በተለይም በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች ከሚደርስባቸው ጥቃት ለመጠበቅ ዓለም አቀፉ ተቋም የሚዘረጋቸው አሰራሮች እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

ኔልሰን የተባለ ተቋም በሰራው ጥናት መሰረት ሰባ አራት በመቶ የሚሆኑ የአትሌቲክስ ደጋፊዎች የዓለምን አትሌቲክስ በበላይነት የሚመራው ተቋም የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ቁርጠኛና ተጨባጭ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ያምናሉ። በዚህም ደስተኛ መሆናቸውን የገለፁት ኮ፣ የዓለም አትሌቲክስ ከፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ እየወሰደ የሚገኘውን እርምጃዎች ከግብ ለማድረስ ሁሉም የአትሌቲክስ ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ቱፋ ሻይ እና ልጆቹ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ:- የቤት ቁጥር አዲስ , ሰበታ, ኦሮሚያ ልዮ ዞን, ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM/13630/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 19/05/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት:-<br>NATI | 4 | የምልክቱ መግለጫ:-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 17 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የፕላስቲክ እቃዎችን መያዣ ምርት (ምድብ 17) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን።ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-180 30/6/2015 (9/3/2023**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ቱፋ ሻይ እና ልጆቹ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ:- ወረዳ ሰበታ የቤት ቁጥር አዲስ, ኦሮሚያ ልዮዞን, ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM/13632/2015<br>ማልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 19/05/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት:-<br>ABEM | 4 | የምልክቱ መግለጫ:-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 17 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የፕላስቲክ እቃዎችን መያዣ ምርት (ምድብ 17) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል።ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-180 30/6/2015 (9/3/2023**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍባለሙብት ሬንጀር ኢንዱስትሪ እና ትሬዲንግ እና በፍ/ባለዕዳ ቻይና ሀንጁን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 00898 /299869 በ23/12/2014 ዓ.ም እና ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የፍ/ባለመብት ግቢ የሚገኝ የሠ/ቁ A03102 ኢት የሆነ ተሸከርካሪ የሐራጅ መነሻ ዋጋ 1,500,000 (አንድ ሚሊዬን አምስት መቶ ሺ ብር ) ሆኖ የጉምሩክ ዕዳ ብር 600,040,07 ያለበት ሆኖ የስም ማዞሪያ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዚያ 4 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል።

የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡2ኛ የሠ/ቁ 3-A63955 አ.አ የሆነ ተሸከርካሪ የሐራጅ መነሻ ዋጋ ብር 2,000,000.00 (ሁለት ሚሊዬን ብር) ሆኖ ተጠቃቃሽ መዝገቦች ያለበት መሆኑ ታውቆ ሚያዚያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም በ4፡30 የስም ማዞሪያ ገዥ የሚከፍል ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል። የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ c.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**